3318



# ፈለገ ብርሃን

(የዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ የሕይወትና የአገልግሎት ታሪክ)
1944 - 2000

ሁለተኛ እትም

በ

ወንድዬ ዓሊ

2002 ዓ.ም

# ፈለገ ብርሃኑ

*. . . በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን (መዝ35:9)*

ኮምፒዩተር፡- ማህደረ ወንድዬ
ከቨር ዲዛይን፡- ፊሎ የማስታወቂያ ስራ





ፈለገ ብርሃኑ
የዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ የሕይወትና የአገልግሎት ታሪክ
1944 -2000
ደራሲ፡ ወንድዬ ዓሊ
አሳታሚ፡- ኢክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት
**Felege Berhanu**
*A Biography of Dr. Berhanu Habte*
*Author: Wondiye Ali*
*Copyright©2010 Arise Ekklesia*
*All rights reserved no portion of this book may be reproduced in any form what so ever, except for brief quotations, in reviews, with out the written permission of the publisher.*

አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር ከዚህ መጽሐፍ ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት፣ በኤሌክትሮኒክስ ውጤቶች መቅረጽና ማራባት የተከለከለ ነው።

አሳታሚ፡- ኢክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት
አድራሻ፡- ስልክ ቁጥር፡ 251116613064
ሞባይል 251911898375
Email: almaz_tarekegn@yahoo.com
P. O. Box: 5903
Addis Abba, Ethiopia

## ማውጫ

ገፅ


መቅድም ........................................ vii
መግቢያ ........................................ x
ጥቂት ቃል ........................................ xiii
የአዘጋጁ ማስታወሻ ........................................ xv
1. በመጀመሪያ - የፍፃሜዉን ........................................ 1
1.1. የቅርብ ሰዉ ቃል ........................................ 1
1.2. የጉዞው ዋዜማ ........................................ 3
1.3. ሰዓቱ ደረሰ........................................ 9
1.4. ጵኒኤል በኤሉሄዉ ሳምንት........................................ 15
1.5. በሱባዔው ማግሥት........................................ 17
1.6. «ጊዜ የለኝም!» ........................................ 18
1.7. የመጨረሻዎቹ ቀናት ........................................ 20
1.8. የካቲት 7፡ ዜሮ - ሰዓት........................................ 22
2. ሰውዩዉ........................................ 25
2.1. አጅሬ፡ ቀበቶ ምሣዉ - ቀበቶ ራቱ! .. 25
2.2. «የቀበቶ ምሣው-ቀበቶ ራቱ ልጅ»... 28
2.3. የልጅ ልባም........................................ 35
2.4. ቤተ መንግሥት........................................ 38
2.5. <ዩንቨርሲቲ>........................................ 41
3. ክርስቲያን ብርሃኑ........................................ 47
3.1.«በልጅነታችን አገኘን»........................................ 47
3.2. የመሠራት ጊዜ፦........................................ 49
3.3. የአገልግሎት ሀ-ሁ . . . ........................................ 51
3.4. ከውጪ ወደ ውስጥ ማየት........................................ 58
4. አገልጋይ ብርሃኑ ........................................ 65
4.1. የመጀመሪያ ጥሪ - 1964 ........................................ 65
4.2. የመጀመሪያዉን ጥሪ የተጫጫኑት... 66
5. ዘመነ መብሰክሰክ (1967- 1983)........................................ 69
5.1. ክርስቲያን ሰው ነው ........................................ 69
5.2. የተቃውሞዉ ቅኝት........................................ 70
5.3. ዘመነ ደርግ - መባቻ ........................................ 72
5.4. ስደት - በኮሚዩኒዝም አርጩሜ........................................ 73
5.5.የቅዱሳን ዕምባ ምርኮና ብዝበዛ ........................................ 78
6. በጥቂቱ የታመነ ........................................ 84
6.1. ባሌ - በጥቂቱ (1967 — 1970)........................................ 84
6.2. ኑሮ በባሌ........................................ 90
6.3. ክርስቲያናዊ ሕብረት - በጎባ........................................ 92
6.4. የሕቡዕ አገልግሎት ማዕከል በጎባ........................................ 96
6.5. ሥራ በባሌ........................................ 100
6.6. ከአናብስት አፍ........................................ 106
7. ከጠርዝ ወደ ጠርዝ........................................ 113
7.1. መሸጋገሪያዉ - አዲስ አበባ........................................ 113
7.2. ስኮት ላንድ - ግላስኮ........................................ 119
7.3. መንፈሣዊ አገልግሎት - በስኮትላንድ 122
7.4. ወደ አገር ቤት........................................ 127
8. ፍቅርና ትዳር ........................................ 131
8.1. እህልና - ውኃ አገጣጣሚ........................................ 131
8.2. «እምባ መድኃኒት ነው»........................................ 140
8.3. ኄዋኔ መጣች........................................ 141
8.4. ጋብቻ........................................ 144
8.5. የጎደ ነገር........................................ 148
8.6. ሰባት ዓመት እንደ 7 ቀን........................................ 150
8.7.ትዳርና - ኑሮ........................................ 152
8.8. አባ ወራዉ ብርሃኑ........................................ 159
9. ጨለማው ሲገፈፍ ጥሪዉ ደመቀ........................................ 169
9.1. ጨለማው ነጋ ........................................ 169
9.2. ጥሪዉ ደመቀ........................................ 171
10. እንደገና በዕምባ ጭጋግ........................................ 178
10.1. ሁሉም በዘመን ጥላ ሥር........................................ 178

*10.2. የማይረሱ ቀናት* ........................ 182
*10.3 ደረቅ ሌሊቶች*........................... 186
*10.4. መለያየት* ............................ 195
*10.5. የመነቀል ጊዜ* ........................ 197
11. ወደ ከበረዉ ሠረገላ............................ 199
*11.1. ነፍሴን መለሳት*........................ 199
*11.2. ‹‹ለእልማዝ ነገርኳት››*.................. 203
*11.3. ከቤት ወደ ዉጭ*........................ 205
*11. 4. ‹‹ደህና ሁኝ ሹመቴ››*................. 210
*11.5. ሽኝት* ................................ 214
12. ራእይና አድማሱ ............................ 217
*12.1. ጥሪዉ - እንደ ባርናባስ*................ 217
*12.2. የአገልግሎት አድማስ*.................... 222
*12.3. የመድረሻው መነሻ* ..................... 223
13. ኤክሌሺያ ተነሺ፡-.............................. 229
*13.1. አነሣሥ እና መስፋፋት*.................. 229
*13.2. የአገልግሎት ስልትና ጥሪት*.............. 234
*13.3. አስተምህሮ*............................ 243
14. አጭር ምዕራፍ፡ የአጭር ዕድሜ መቋጫ...... 263
*14.1. ‹‹ሃይጃክ!››*........................... 263
*14.2. የበረከት ጉድጓድ*....................... 266
*14.3. ሰበብ*.................................. 269





# መቅድም

***‹‹የጻድቃን ሞት እኔ ልሙት፤ ፍጻሜዬም የእርሱ ዓይነት ፍጻሜ ትሁን!›› (ዘኁ. 23፡10)***

ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጣቸው አዲስ ሕይወትና የከበረ አገልግሎት ሕያው ምሳሌና ታማኝ ሎሌ በመሆን በመካከላችን በትልቅ ትሕትናና ጥልቅ በሆነ ፍቅር በቅድስናም ሕይወት በመመላለስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሲያስተምሩ፣ በልዩ ልዩ መልክ ሲያገለግሉ፣ ሲመሩ የኖሩት ውድ ወንድማችን ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ በምድራዊ ጉዟቸው ሊያከናውኑት የተገባቸዉን ሙያዊና መንፈሳዊ አገልግሎታቸዉን ፈጽመዉ ወደ ሚወዱትና ወደ ሚናፍቁት አምላካቸዉ በክብር ከተሰበሰቡ ሁለት ዓመት ሆናቸዉ።

ዶ/ር ብርሃኑ በአርባ ዓመታት የክርስትና ሕይወት ጉዟቸው በርካታውን ጊዜ ያሳለፉት የብርሃነ ወንጌል መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያንን በመምራት፣ በማደራጀት፣ በማስተማር፣ ወንጌልን በመስበክና በልዩ ልዩ አገልግሎት ዘርፍ በትልቅ ትጋትና በምሳሌነት በማገልገል ነበር።

ለእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ሕይወታቸዉን በሙላት የሰጡት ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ ዛሬ በአካል ቢለዩንም አብረዉን ባሳለፏቸው ወርቃማ የአገልግሎት ጊዜያት፡- በቅንነት፣ በጽድቅና በፍቅር በተሞላ ሕይወታቸዉ የፈጸሙት ተግባራትና ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባራቸዉ ሁሌም በፊታችን ተስሎ ስለሚታየን ዛሬም አብረዉን እንዳሉ ሆኖ ይሰማናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ዛሬም የእርሳቸዉን የሕይወት ዓርዓያነት በመጠቀም በልዩ ልዩ መንገድ በግልና በሕብረት እያስተማረን፣እየተናገረንም ይገኛልና።

አሁን ደግሞ የአገልግሎታቸዉና የሕይወት ምስክርነታቸዉ በወግ ተደራጅቶ በመጽሐፍ መልክ ለእኛ በቅርብ ለምናውቃቸዉም ሆነ አገልግሎታቸዉ ላልደረሳቸው ወገኖች ሁሉ ትምህርትና መልካም መልዕክት እንዲሆን መቅረቡ አገልግሎታቸዉ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርግ ለሁላችንም የተሰጠን ጠቃሚ ዕድል እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህም መልካም መከናወን ሁሉን ያዘጋጀውን እግዚአብሔር አምላካችንን እናመሰግናለን።

እግዚአብሔር በአንድ ሰው ሕይወት አማካኝነት ብዙ ትውልዶችን ማገልገል ያውቅበታል። ይህንንም ሲያደርግ በታማኝነትና በቅንነት ብዙ ዋጋ ከፍለው ያገለገሉትን የታማኝ ባሪያዎቹን ሕይወት ሁሌም የክብሩ፣ የፍቅሩና የበጎ ዓላማው መገለጫ አድርጎ በመጠቀም ነዉ። ለዘህም የእግዚአብሔር ቃል እና በምድር ላይ በሕይወት በኖሩበት ዘመን በፈጸሙት አገልግሎት ትውልድን የሚያስተምርና የሚያንፅ አሻራ ትተው ያለፉት ቅዱሳን አባቶችና እናቶች ታሪክ ምስክር ነዉ። ዛሬም በዚህ የሕይወት ታሪክ መጽሐፍ አማካኝነት በታማኝ ሎሌው ሕይወት ሊያስተምረንና ሊቀርጸን ወዶ ለትውልድ የሚተላለፍ መልእክት ያዘጋጀልንና መልካም ዕድልን ያመቻቸልን እግዚአብሔር ይመስገን።

ይህ የዶ/ር ብርሃኑ የሕይወት ታሪክ፣ የአገልግሎትና የሥራ ዘመን ምስክርነት መጽሐፍ በኢትዮጵያ ብርሃነ ወንጌል መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያን ለምንገኝ ምዕመናን፣ ለመሪዎችና ለአገልጋዮች፣ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትና በሌሎችም ክርስቲያናዊ ቤተ እምነት ለሚገኙ የክርስቲያን ማሕበረሰብ፣ መሪዎችና የወንጌል አገልጋዮች ሁሉ የተሰጠን ትልቅ ዕድል ስለሆነ መጽሐፉን አስተውለን ልናነበው፣





በወንድማችን የሕይወት ምስክርነት ዛሬም ልንገለገልና ልንጠቀምበት ይገባናል።

የወንድማችን የዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ የግል የሕይወት፣ የሥራና የአገልግሎት ዘመን ታሪክ ለንባብ እንዲበቃ ታላቅ ጥረት የአደረጉትን "የኤክሴሺያ ተነሺ!" አገልግሎት የባላደራ ቦርድ አባላትን፣ በዝግጅቱ ሂደት የተሳተፉትን ወገኖች፣ የአገልግሎቱ ዋና አጋር የነበሩትንና በዚህም የመጽሐፍ ዝግጅት ሂደትም ወሳኝ ሚና የተጫወቱትን ውድ ባለቤቱን፣ ልጆቹንና መላው ቤተሰቡን፣ በተለያየ መንገድ ለአገልግሎቱና ለዚህም መልካም ሥራ ተባባሪ የሆኑትን ሁሉ እግዚአብሔር አምላክ ይባርካችሁ፤ ብድራታችሁን በመልካም ይመልስላችሁ በማለት ልባዊ ምስጋናችንን በአክብሮት እናቀርባለን።
ይህንን በድጋሚ የተሰጠንን መልካም ዕድል በአግባቡ እንድንጠቀምበትና በሕይወታችንና በአገልግሎታችን እንድናድግበት፣ ሌሎችንም በምሳሌነት እንድናገለግልበት አምላካችን እግዚአብሔር ለእኛም ትጋትንና ታማኝነትን ቅንነትንና አስተዋይነትን ይስጠን። ምሕረቱንና ጸጋውንም ያብዛልን።

*ሁሉን ላዘጋጀዉ ለእግዚአብሔር*
*አምላካችን*
*ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብርና ምስጋና*
*ይሁን።*
*አሜን*

መጋቢ ፈቃዱ ታደሰ
የኢትዮጵያ ብርሃነ ወንጌል መጥምቃውያን
ቤተ ክርስቲያን - ዋና ጸሐፊ

# መግቢያ

የአንድ አገር ታሪክ በየተሠማሩበት ዘርፍ ዘመን ተሻጋሪ ድርጊት ከአከናወኑ ግለሰቦች ድምር ገድል ተወስዶና ተቀናጅቶ የሚቀርብ ነው። በአንፃሩም የቤተክርስቲያን ታሪክ የሚዋቀረዉ በክርስቶስ የማዳን ሥራ ላይ ተመሥርተዉ ቅዱሳን የተጠሩበትን የወንጌል ባለአደራነት ለመፈጸም ሲሉ የከፈሉትን መስዋዕትነት፣ በሕይወታቸው የተፈጸሙትን ድንቅና ተዓምራት እንዲሁም የተገኘዉን መንፈሳዊ አዝመራ ከሚተርኩ የታሪክ ማስታወሻዎች ነው። ስለሆነም በየትኛውም መልኩ በጽሑፉ ሠፍረው ለትውልድ የሚቀመጡ ታሪኮች ከምንገምተዉ በላይ ዋጋቸዉ ከፍ ያለ ነዉ።

የወንጌል ዘር አገራችን ውስጥ በቅሎ ለዚህ ደረጃ የበቃው በብዙ መከራ እንደሆነ ይታወቃል። በዚያዉ ልክ ስለወንጌል ሲሉ የዚህን ዓለም ብልፅግናና ክብር የናቁ፣ ሕይወታቸውን ጭምር መስዋዕት የአደረጉ የመከራው ገፈት ቀማሾች በርካቶች ናቸው። ይሁን እንጂ ታሪካቸው በውል ባለመመዝገቡ ወይም በመድበስበሱ ምክንያት ከድላቸውና ከውድቀታቸው በሙልዓት እንዳንማር ገደብ ሆኖብን ቆይቷል።

ይህንን ገደብ ለመሻር የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የቤተእምነቶቻዉንና የቀዳሚ አገልጋዮቻቸውን ታሪክ ለማዘጋጀት በተለይም ከአለፉት አስራ አምስት ዓመታት ወዲህ ያሳዩት መነሳሳት ተስፋ ሰጪ ነው። ጥረታቸው ሲሰምር ፈረንጆቹ ‹‹ያልተዘመረላቸው ጀግኖች›› የሚሏቸውን ዓይነት የወንጌል አርበኞች የታሪክ አሻራ ጋ' እንደምንተዋወቅ ጅምሩ አመላካች ነው። ኤክክሌሺያ ተነሺ አገልግሎትም ይህንን የዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴን የሕይወትና አገልግሎት ታሪክ ለማሳተም ሲበቃ ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በማገናዘብ ጭምር ነው።





የዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ ሕይወት ከልጅነት የምድር ቆይታቸዉ እስከ አበቃበት ድረስ በብዙ ቁም ነገሮችና ስኬቶች የታተመ ነዉ። አርዓያነቱንም፡- ልባም ልጅ፣ ጎበዝ ተማሪ፣ ሥራ ፈጣሪ፣ ለጌታዉ ያደረ፣ ግሩም ባለሙያ፣ ተመራማሪና አስተማሪ፣ ጠንቃቃ የሥራ መሪ ... የሚሉት ሐረጎች በአጭሩ ሊገልጡት ይሞክራሉ።

ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ ለዚህ ሁሉ ቁም ነገና ስኬት ያበቃቸውን ጌታ እግዚአብሔርን ሁለንተናቸውን ሰጥተዉ ለማገልገል ሲሉ ባለጸጋ መሆን ሲችሉ በፈቃዳቸዉ በዝቅተኛ ኑሮ ለመኖር የወሰኑና የኖሩ ናቸዉ። ... በዚህም ፍጹም የማይፀፀቱ ናቸዉ። ይህንን የመሰለ ዓርዓያነት የተሞላዉ የሕይወት ፈለግ በባለታሪኩ ቤተሰብና በቅርብ ሰዎቻቸዉ ብቻ ተወስኖ ለምን ይቅር?

እንደሚታወቀዉ ፈጣን ሯጮች የተተለመላቸዉን ርቀት በፅናትና በፍጥነት ሮጠዉ ሲያጠናቅቁ የተዘጋጀላቸዉን ሽልማት ቀድመዉ ይጨብጣሉ። ይህም የሚጠበቅባቸዉን ተግባር ያለምንም መዘናጋትና ማመንታት ያላቸዉን ኃይል ሁሉ ተጠቅመዉ በፅናት በማጠናቀቃቸዉ ነዉ። ዶ/ር ብርሃኑም የተቀበሉትን አደራ እንደ ተሰጣቸዉ ጸጋ መጠን በአጭር ጊዜ ስላጠናቀቁ ወደ እረፍታቸዉና ወደ ሽልማታቸዉ ቦታ ቀድመውን ሄደዋል። የእግዚአብሔር አገልግሎት በአንድ ሰዉ ዕድሜ ተሰርቶ የሚጠናቀቅ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም እስኪገለጥ ድረስ የሚቀጥል እንደ መሆኑ፡- የእኒህ የእግዚአብሔር ሰዉ ፅናት የተሞላዉ የወንጌል ሩጫና ጥንቁቅ የአኗኗር ዘይቤ ምስክርነት ከእርሳቸዉ በኋላ ለሚነሱት አገልጋዮች ሁሉ ትምህርት እንደሚሆን በመታመኑ ነዉ ታሪካቸዉ ለአንባቢያን እንዲደርስ የተወሰነዉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ጥንካሬዎቻቸዉ ብቻ አይደለም አንባቢዎች ከዶ/ር ብርሃኑ የሕይወትና የአገልግሎት ታሪክ የሚማሩት፤ በመጽሐፉ ዉስጥ በቀጥታና በእግረ መንገድ ከተገለጹት የግል ምርጫዎቻቸዉና ውሳኔዎቻቸዉ እንዲሁም ከማሕበራዊ ግንኙነት ምልከታቸዉ አንፃር እንደ ማንኛዉም ሥጋ ለባሽ አከራካሪ ከሚመስሉት እርምጃዎቻቸዉም እንጂ።

በተጨማሪም ባለታሪኩ በአጠቃላይ በወንጌል ሥራዎች ዙሪያ በተለይም ደግሞ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ራዕይ ተግባራዊ ከማድረግ ረገድ የአዘጋጁቸዉ ከአስር በላይ መጻሕፍትና የማሠልጠኛ መምሪያዎች፣ እንዲሁም በርካታ የጥናት ወረቀቶች መካከል የተወሰኑቱ ተጨምቀዉ በመቅረባቸዉ ይህ የሕይወት ታሪካቸዉ ዝግጅት ለሥነ መለኮት ተቋማት፣ ለወንጌል ተልዕኮ አገልግሎቶችና ለክርስቲያናዊ ድርጅቶች የሚኖረዉ አስተዋፅዖም ከፍተኛ እንደሚሆን እናምናለን።

በመጨረሻም ይህንን የሕይወት ታሪክ ዝግጅት መርሐ ግብር በተመለከተ ቅድመ ሃሳቡን ከማፍለቅ ጀምሮ፣ በጸሎት፣ በምክር፣ በበጀት ድጎማ፣ በሙያዊ ተሳትፎ፣ እንዲሁም ረቂቁን በማንበብ፣ እርማትና አስተያየት በመስጠት የተሳተፋችሁትን ሁሉ በኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት ስም ላመሰግን እወዳለሁ። እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ።

*እነሆ ፈለገ ብርሃኑ*

*ለእግዚአብሔር ክብር ለሰዉም ጥቅም ይሆን ዘንድ*

*በ2002 ዓ.ም ታተመ።*

አታላይ ዓለም (ዶ/ር)

የኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎት ባላደራ ቦርድ ሰብሳቢ





# ጥቂት ቃል

ለብዙ ሰዎች 'ዓላማ' ከቃልነቱ ያለፈ በሕይወት ጉዞአቸው የተገናዘበ ትርጉም የለውም። የአንዳንዶቻችን የሕይወት ታሪክ ሽለቆ ደርሶ መቆም እንደተገደደ ከተራራ አናት ላይ እንደ ተፈነቀለ ዓለት ከዕለት ወደ ዕለት ከማናልፈው ሞት እስከምንደርስ ድረስ እንደ መንከባለል ያለ ሂደት ነው።

ሌሎቻችን ደግሞ ሕይወታችንን በዓላማ የምንመራው እንኖርበታለን ያልነውን ዓላማ የሚገዳደሩ ሁኔታዎች እስካልገጠሙንና ኑሮ 'አልጋ በአልጋ' እስከሆነልን ድረስ ነው። ዓላማቸውና ግባቸው 'አድሮ መገኘት' ከሆነውና በየምዕራፉ ተግዳሮት ሲገጥማቸው 'ጎመን በጤና' እያሉ መንገድ ከሚቀያይሩት ለየት ያለ *ለዓላማቸው የጨከነ ማንነት* ያላቸው ጥቂት ሰዎች አሉ።

ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ ለዓላማቸው የጨከነ ሕይወት ካላቸው ጥቂት ሰዎች አንዱ ነበሩ። የዚህን የሕይወትና የአገልግሎት ታሪክ መጽሐፍ ዝግጅትና ሕትመት የመከታተል ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ቡድን አባላት ዶ/ር ብርሃኑ በሕይወት ዘመናቸው ሳሉ የኖሩትን የሕይወትና ይሰጡ የነበሯቸውን አገልግሎቶች የተወሰኑ ልዩ ልዩ ገጽታዎች የምናውቅ ነን። ሆኖም ከተጣለብን አደራ አንፃር የዚህን መጽሐፍ ዝግጅት ስንከታተል ዶ/ር ብርሀኑ ያሳለፏቸውን የሕይወት ገጠመኞችና የአገልግሎት አድማሳቸውን ለመመልከት፣ ለመደነቅና እግዚአብሔርም በርሳቸው ሕይወት ተጠቅሞ ስለሠራው ታላቅ ሥራ ለማመስገን ዕድል አግኝተናል።
ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኝና ጌታ አድርገው የተቀበሉት ገና በለጋ የወጣትነት ዕድሜያቸው ነበር።

በጌታ በኢየሱስ አዲስ ሕይወት አግኝተው ከተለወጡበት ጊዜ ጀምሮ ግን እግዚአብሔርን ማምለክና ማገልገል የሕይወታቸው ተቀዳሚ ዓላማ ሆኖ እስከ ብፁዕ ስንብታቸው ዕለት ዘልቋል። ዶ/ር ብርሃኑ በሕይወት ዘመናቸው ጉልህ ስፍራ ይዞ ለነበረው የወንጌል አገልግሎት ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ለማገልገል እስከወሰኑበት ዕለት የብዙዎቻችንን ሕይወት በሚያማልሉና በሚያስቀኑ በርካታ ምድራዊ ከፍታዎች አልፈዋል።

ምስጉን፣ ምሑር፣ የተደነቁና የተወደዱ የኩላሊት ሕክምና ስፔሺያሊስት፣ የውስጥ ደዌ ረዳት ፕሮፌሠር፣ የሕክምና ፋክልቲ ዲን፣ እንዲሁም ተባባሪ ፕሮፌሰር መሆን ሊያስገኙላቸው የሚችለዉን ክብርና ጥቅም ሰውተው በሙሉ መሰጠት ወንጌልን አገልግለዋል። "ኤክሌሺያ ተነሺ!" በሚል መሪ ቃል ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበሉት ራዕይ መሠረት ምሳሌያዊ የሆነ የደቀ-መዝሙርነት ሕይወት በአማኞች መካከል እንዲሰፍንና ቤተ ክርስቲያንም በዚህ የመጨረሻ ዘመን በድል እየገሰገሰች የተሰጣትን ተልዕኮ በሚገባ እንድትፈጽም በአገር ውስጥ ከአገር ውጪም በአብዛኛዎቹ ክፍለ አህጉራት ትምህርትና ሥልጠና በመስጠት ለቀጣዩ ትውልድ የሚሆን ቅርስ ትተው አልፈዋል።

ይህንን መጽሐፍ ስታነቡ ለእግዚአብሔር ዓላማ በጨከነ ማንነት እግዚአብሔር ምን ሊሠራ እንደሚችል ትገነዘባላችሁ። ምሳሌያቸውንም ለመከተል በእግዚአብሔር ፀጋ ትነሣሣላችሁ ብለን እናምናለን።

ሚናስ ብሩክ
ንጉሤ ቡልቻ
*የሕይወትና የአገልግሎት ታሪክ መጽሐፍ ዝግጅት*
*የሥራ ቡድን አባላት*





# የአዘጋጁ ማስታወሻ

**የዕምባ ፍሬ?!**

ከአስር ዓመታት በፊት ሰኔ ወር 1992 ዓ.ም ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ የዚህን ጸሐፊ ቤትና ቤተሰብ ጎብኝተዉ ነበር። ወቅቱም የነበራቸዉን ሥልጣንና ውድ ሙያ ትተዉ ለሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይነት ራሳቸዉን መስጠታቸዉ በክርስቲያን ማህበረሰቡ ዘንድ ዋና መነጋገሪያነቱ ገና ያልበረደበት ወራት ነበር። በሌላ በኩል በእምነት ነፃነት ማግሥት በወንጌላዉያን ማሕበረሰብ ዙሪያ የተነሣዉ መደፈራረስ ገና ያልጠለለበት ሰሞን እንደ መሆኑ ጸሐፊዉም እንደ ብዙ መሰሎቹ የፀለምተኛነት ዳመና ተጫጭኖት ነበርና ‹‹ይህንን ያህል ትልቅ ባለሙያ እንዴት በዚህ ወቅት ራሱን ፈተና ምድጃ ላይ ይጥዳል?›› ሲል በዉሳኔያቸዉ የተደናገረበት ሰሞን ነበር።

ዶ/ር ብርሃኑ ሥራዬ ብለዉ የመጡበት ጉብኝት ነበርና ራዕያቸዉን አካፈሉት፤ ከዚያም የዉሳኔያቸዉን ትክክለኛነት አረጋገጡለት፤ ቀጥሎም አስተያቱን ጠየቁት። ጸሐፊዉም በትሁት ቀጥተኛነት፡- *‹‹ከዚህ ቀደም ለእኛ ለኢትዮጵያዉያን የሰጠንን ባለራዕዮችንና ራዕያቸዉን የበላ ጅብ ሳይጮህ ሌላ ባለራዕይ ‹እንበላ› ዘንድ እግዚአብሔር መፍቀድ ያለበት አይመስለኝም››* አላቸዉ። አያይዞም፡- *‹‹ለመሆኑ እርስዎ ይህንን መስዋዕትነት ለመክፈል ሲወስኑ በእዉነት ኢትዮጵያ የመታደስ ተስፋ እንዳላት እርግጠኛ ነዎትን?››* ሲል ጠየቃቸዉ።

በዘወትር እርጋታቸዉ አንገታቸውን ወደ እርሱ ዘመም አርገዉ በሰርሳሪ ዓይኖቻቸዉ ለሰከንዶች ያህል ተመለከቱት። ለጊዜዉም የዉስጥ አካላትን ምስል በሚያነሳ መሣሪያ (ኤክስሬይ) ዓይነት

ነገር የመበርበር ስሜት ተሰማዉ። *‹‹ወዳጆ! ኢትዮጵያ የመታደስ ተስፋ የማይኖራት ከሆነማ ምን ያንከራትተኝ ነበር?! ... ››* ሲሉ መለሱለት። ከለስላሳ አንደበታቸዉ ከወጡት ቃላት ይልቅ ከገፅታቸዉ ያነበበዉ መልእክት ግን ከባድ ነበር። *‹‹አንተም! ... አንተም አልተረዳኸኝምን!?››* ብሎ ለራሱ ተርጉሞታልና።

ዳግም በአካል ሳይተያዩ ከረሙ። የሕልፈታቸዉን መርዶ ሰማ። በዓመቱ የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም ታሪካቸዉን እንዲጽፍ ተጋበዘ። ሙያዉ በሚጠይቀዉ ስልት ጥናትና ምርምሩን ጀመረ። መረጃዎችን ሲያገላብጥ - ሲመረምር ከዓመታት በፊት ከኤክሴሺያ ተነሺ አገልጋዮች ጋር ስለ እሱ የማለዱበትን የዐዉደ ዕለት ማስታወሻ አገኘ። በከፊል እንዲህ ይነበባል፡-

> *‹‹ከዶ/ር ------------ ሌላ ተስፋ ቆርጠዉ ካገኘኋቸዉ ሰዎች መካከል አንዱ ወንድዬ አሊ ነዉ። የመታደስ ተስፋ አለ ብለህ ታምናለህን? ሲል ጠየቀኝ። ... አዎ! ሙሉ እምነት አለኝ። በሕይወት የምኖረዉ በዚሁ ምክንያት ነዉ። ... እንዲያዉም የበኩሌን አስተዋፅዖ ለማድረግ ጥድፊያ ይሰማኛል! ብዬ በእምነት ተሞልቼ መለስኩለት።›› (ዐውደ ዕለት ሰኔ 25 ቀን 1992)*

የወዳጆቹን ምልጃ የማይረሳዉ ጌታ አምላክ ዘመኑን ቆጥሮ የጸሐፊዉን ጥርጥር በልዝብ ልምጩ ቀጣ። ይኼዉ በባለራዕዩ በኩል ምድሪቱ ላይ የጣለዉን የተሃድሶ መሠረት ለሌሎች ለመመስከር እና የሕይወት ታሪካቸዉን ለመጻፍ በቃ።





**የሕይወት ታሪክ የመጻፍ ፈተና**

የኔ ቢጤዉን ተራ ሰው ታሪክ መጻፍ በእዉነቱ አስጨናቂ የቤት ሥራ አይደለም። *‹‹በዚህ ዘመን ተወልዶ፣ በዚህ ጊዜ አረፈ። ይህን ያህል ዓመት ሥራ ላይ ቆይቷል። ክርስቲያንና የአንድ ሚስት ባል፣ የሁለት ልጆች አባት ነበር!››* ይባልለታል። አለቀ - ደቀቀ። ከመቃብር በላይ የሚሞግት ስም የለው፣ ገድል የለው፣ ከሣሽ የለው - ወቃሽ የለው። የዶክተር ብርሃኑ ሀብቴን የመሰለ ባለ ብዙ ፈርጅና ቀለማት የሕይወት ሂደት ፈሩን ተከትሎ ወደ ፊደል መለወጥ ግን ፈተና የተሞላበት ሥራ ነው።

በምሣሌ ማስረዳቱ ይቀል ይሆን? ስለ ቀስተ ዳመና ምንነት እና ቀለም የኔ ቢጤውን እንዲያስረዳ ቢጠይቁት ‹‹... የማርያም መቀነት አይደለች? ... ናት እንጂ! ልክ ባንዲራችንን ትመስላለች!›› ብሎ ይገላገላል። የተፈጥሮ ዉበት የገባዉ ሰብዕ ከሆነ ግን ከፈጠጡት ቀለማት በስተጀርባ በረቂቅ የዉበት መስመሮች የተጣመሩትን የብርሃን ፈርጦች፡- ድቀት፣ ዉኅደት፣ ተምሣሌትነት፣ እንዲሁም አንደምታቸዉን ከነስር መሠረታቸዉ መግለጫ ቃላት እስኪአጥረዉ ድረስ ያትተዋል።

የዶ/ር ብርሃኑ ሕይወት እንዲሁ፡- በአንድ በኩል ግልፅ፣ የሚታይና የሚጨበጥ ነዉ። በሌላ በኩል ረቂቅ የሕይወት ቀለማት ውኅድ ነው። ለሁሉም እንደ ዓይነ ልቡናዉ አቅም መጠን የሚገለጥ - የሚሰወርም ነው። የታመቀም፣ የተዘረዘረም ነው። ስለሆነም ልክ እንደ ማርያም መቀነት፡- ያለ ምንም ጥያቄ ጠቅልለዉ ወይም የደመቀላቸዉን ያህል መርጠዉ ሊላበሱት የሚወዱ የመኖራቸዉን ያህል አከራካሪ ውኅዱ

እየተፈታተናቸዉ በሩቁ ቆመዉ ብቻ እንዲታዘቡት ያደረጋቸዉ አይጠፉም። አንዱም ይህ ጸሐፊ እንደ ነበር ቀደም ሲል ተናሟል።

ነገር ግን ጠጋ ብለዉ ሲመረምሩት የዶ/ር ብርሃኑ የሕይወት ጉዞ ዘርፈ ብዙ ቀለማት ያሉት ቢሆንም ኅብሩ አንድ ወጥ ነው። እምነት፣ መሰጠት፣ ቀጥተኝነት ነዉ። ልባምነት፣ ምልስነትና ባለአዕምሮአዊነትም ነዉ። የዓላማ ቁርጠኝነት፣ የጥንቁቅነትና የትጋት ቅምር ነው። እውነት፣ ንፅህና፣ ትህትናና ርኅራኄ ነው። ዓላማዉም የሰዉን ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ማገልገል ብቻ ነዉ። ለዚህም የይሉኝታ፣ የባህልና የወግ፣ የጥቅምና የክብር ቀለበቶች ተደማምረዉ የሚሠሩት ቅጥልጥል ሰንሰለቶች አሥረዉ የማያቆሙት ገታራ ሕይወት ነዉ። ይህም ከቤተሰብ አስከ አደባባይ ድረስ ዘልቆ የተገለጠ ሕይወት ነዉ።

ይሁን እንጂ እንደ ‹ብዙነቱ› የተበተነ አይደለም። በባለታሪኩ የግል የሕይወት ፍልስፍናና የአኗኗር ሥርዓት በጥንቃቄ የተደራጀ ነዉ። ስለሆነም መዝገቡን ከፍቶ ቅጠሎቹን ሳይሆን፣ እንጓዎቹን መርጦ ማገጣጠሙ፣ እንዲሁም ለመንፈሳዊዉም ለባለአዕምሮዉም ተደራሲ እንደሚመች አድርጎ መዘገቡ የዚህ ጸሐፊ ቀዳሚዉ ፈተና ነበር።

**የሕይወት ታሪክ ግብዓቶች**

ደብሊዉ ኤች አደን (1907 - 1973) የተባለዉ እንግሊዛዊ ገጣሚ የሕይወት ታሪክ መጽሐፍ ዝግጅትን አስመልክቶ ሲናገር፡- *‹‹በሥርዓት ተደራጅቶ የተመራ ሕይወት - እሱ ብቻ ነዉ የተሟላ የሕይወት ታሪክ ግብዓት የሚሆኑ የግል*





*መረጃዎችን የሚነግራችሁ››* ብሎ ነበር። እንዴት ያለ ታላቅ ማስተዋል የተሞላ አነጋገር ነዉ!

የዶ/ር ብርሃኑ የግል የሕይወት አመራርና የአኗኗር ዘይቤ በጥንቃቄ የተሰደረ በመሆኑ አብዛኛዎቹ የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት የጥናትና ምርምር ሥራ መነሻና መድረሻ የሆኑት መሠረታዊ የመረጃ ግብዓቶች ምንጭ የተገኙት ባለታሪኩ ራሳቸዉ ትተዉልን ካለፉት የጽሑፍ ማስታወሻ፣ የፎቶ ግራፍ፣ የሕትመት እና የኤሌክትሮኒክስ ሰነዶቻቸዉ ነዉ።

ከእነዚህም መካከል ከ1964 — 2000 ዓ.ም ያሉትን የሠላሳ ስድስት ዓመታት የባለታሪኩን ዉጣ ዉረዶች ከነሁለንተናዉ ፍንትዉ አርገዉ የሚያሳዩት የዐውደ ዕለት ማስታወሻ መመዝገቢያ (Diary) ጥራዞች ዋነኞቹ ናቸዉ። የጥራዞቹ ብዛት 16 ሲሆን ርዕስ ጉዳይ ማመላከቻዉን (Index) ጨምሮ 2086 ያህል ገፆች ይሸፍናሉ።

**የዐዉደ ዕለት ማስታወሻ ምንድን ነዉ?**

> *‹‹የዐውደ ዕለት ማስታወሻ ለጸሐፊዉ መለኪያ የሌለዉ የቁም ነገር ማኅደር ነዉ። ለዘመን አቻዎቹ ደግሞ በእዉነቱ ትርጉም ላይኖረዉ ይችላል። ለተማሪዎች ጭራሹኑ እርባና ቢስ ጉዳይ ነዉ። ጠብቆ ላቆየዉ ግን ከመቶ ዓመታት በኋላ ብርቅዬ ኃብት ነዉ››*። (ኤለን ቴሪ (1847 — 1928, *The Story of My Life*)

የግል ዐውደ ዕለት ማስታወሻ ሰዎች የጊዜዉን የነፍሳቸዉን *መገረም* በማድመጥ የልቡናቸዉን መረዳት እንደ ወረደ አንጠፍጥፈዉ የሚያሰፍሩበት የግል መዝገብ ነዉ። በሌላ አነጋገር *‹‹በሕይወት ሂደት ከአለፈባቸዉ ወይም ከአሳለፉት ክስተቶች ዉስጥ ልቡናቸዉን ሰቅዞ የያዘዉን ጉዳይ እንደ ዘበት*

*በትኩስ ስሜት የሚተነፍሱበት ለራስ በራስ የሚጻፍ ደብዳቤ ነዉ›› ይሉታል* - የግለታሪክ ጽሑፍ ባለሙያዎች፡፡ ስለሆነም የአንድን ሰዉ ግለታሪክ ለመዘገብ ከባለታሪኩ የዐውደ ዕለት ማስታወሻ የበለጠ ተዓማኒ መነሻ ፈፅሞ አይገኝም ለማለት ያስደፍራል፡፡ ከቶውንስ - ሰዉ ከራሱ ምን ምስጢር ሊሸሽግ ይቻለዋል?

**ምንስ ፋይዳ አለዉ?**

የተለያዩ ሰዎች ለግል የዐዉደ ዕለት ማስታወሻ የሚሰጡት ዋጋ የተለያየ ነዉ፡፡ ምግባራቸዉ ከህሊናቸዉ የተጣረሰባቸዉ ፖሊተከኛ እንዲህ አሉ፡-

> *‹‹እኔ የዐውደ ዕለት ማስታዎሻ መመዝገብ አልወድም፡፡ ዐውደ ዕለት መመዝገብ ማለት ለእኔ የየቀኑን ትውከቴን መልሶ ማሰብ ማሰላሰል ማለት ነዉ፡፡››* (ብሪታኒያዊዉ ፖለቲከኛ ኤኖክ ፖል (1912 - 1998)

ታዋቂዉ ሩሲያዊ ደራሲ ሌዊ ቶልስቶይ ደግሞ ራሱ ለራሱ ለጻፋቸዉ የነፍሱ አሻራዎች የሆኑትን የዐውደ ዕለት ማስታዎሻዎቹን መልሶ ይቀዳድዳቸዉ ነበር፡፡ የሆነዉንና የሆነበትን ለመቀበል አልወደደምና፡፡ በዚህ ባሕርይዉ የተበሳጨችዉ ባለቤቱ ዐውደ ዕለቷ ላይ የሚከተለዉን አሰፈረች፡-

> *‹‹ባለቤቱ ሲመዘግብ የከረመዉን የዐውደ ዕለት ማስታዎሻዎች መልሶ ይቀዳቸዋል፡፡ ... ከዚያም የአባትነት ካባዉን ብቻ ደርቦ (ያልሆነውን ሆኖ) በልጆቹ ፊትና በሕዝብ አደባባይ ሊታይ ይፈልጋል፡፡ በእዉነቱ ትልቅ ስህተቱ ይህ ነበር፡፡››* (ሶፍያ ቶልስተይ (1844 - 1919) የዐውደ ዕለት ማስታዎሻ የተወሰደ)





በራሱና በተግባሩ ለተማመነዉ ብሪታኒያዊዉ ብሔራዊ ጀግና የዐዉደ ዕለት ማስታወሻ ፋይዳዉ ከመቃብር በላይ እንደሚተከል ሐውልት ያህል ታላቅ ነበር፡፡

> *‹‹... በሕይወት ከቆየሁ መልካም፡፡ አለዚያ ግን በዚህ ጉዞ እኔና ጓደኞቼ የገጠመንን ተግዳሮት፣ አይበገሬነታችንን እና የጀግንነታችንን ነገር ለሚመጣዉ ትውልድ የሚተርኩልን እነዚህ በግርድፍ ቃላት የጻፍኳቸዉ የዐውደ ዕለት ማስታዎሻዎቼ ናቸዉ፡፡›› (ከእንግሊዛዊ አሣሽ ሮበርት ፋልኮን (1868 - 1912) ዐውደ ዕለት የተወሰደ)*

እንደ ሮበርት ፋልኮን ሁሉ ዶ/ር ብርሃኑም ትተውልን ያለፉት ቅርስ ከመቃብር በላይ ስለ እሳቸዉ ያለ ምንም ማመቻመች ሊናገርላቸዉ የተገባዉንና ማንነታቸዉን ያለ ስስት የዘረገፉበት የዐውደ ዕለት ማስታወሻቸዉን ነዉ፡፡ እንግዲህ የዚህ መጽሐፍ ዋነኛ የመረጃ ምንጭም ይህ መዝገብ ነው፡፡ በአጭሩ ሰውዬው ወደ አምላካቸው ከመሰብሰባቸው በፊት አውቀዉም ሆነ ሳያዉቁት ታሪካቸውን በግርድፍ ጽፈውት ነበር ማለት ነው፡፡

**የጸሐፊዉ ድርሻስ?**

የዚህ ጸሐፊ ድርሻ ምንድን ነው? ታሪኩን ማመሳከር፣ ለማመሳከርም በርካታ ስልታዊ - የተናጠልና የቡድን ቃለ ምልልሶችንና ውይይቶችን ማድረግ፣ የሕትመትና የኤሌክትሮኒክስ ሰነዶችን መመርመር - አንደኛ፡፡

ሁለተኛም፡- ለዚህ ህትመት ዝግጅት ዓላማ ወጥነት ያላቸዉን መረጃዎች ማገጣጠም፡፡ ሦስተኛም፡- ከወቅቱ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዳራ በተለይም ከጊዜዉ የቤተክርስቲያን ሁለንተናዊ ዐውድ ጋ' አዛምዶ ታሪካዊ ኦንደምታዉን መተንተን፤

በተጨማሪም ሁሌ አግባብ አይሁን እንጂ የግሉን አስተያየቶች መሰንዘር፡፡ አራተኛም፡- ለገዛ ህሊናውና ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ታማኝ ሆኖ፣ የሥነ ጽሑፍ ሥነ ምግባራትን አክብሮ መተረክ፣ ደግሞም ትረካዉን ለዛ ማላበስ ዓይነተኛ ኃላፊነቱ ነበር፡፡

**የአተራረክ ስልት**

የዚህ መጽሐፍ አተራረክ ስልት ሆን ተብሎ የተለመደዉን የታሪክ አጻጻፍ ዘይቤ እንዳይከተል ተደርጓል፡፡ ይልቁንም በይዘት ረገድ ዙረ-ገብ እንዲሆንና በአንድ ጥራዝ እንደ ሚታተሙ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ስብስብ (Collection of Literary Works) ራሳቸውን በቻሉና በየትኛውም የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ መሳግ (መከተት) በሚችሉ የምዕራፎች ኅብር እንዲዋቀር አዘጋጁ ፈርዶበታል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ባለታሪኩን ልዩ የሚያደርጓቸዉን አንኳር የሕይወት ገፅታዎች አጉልቶ ለማሳየት እንዲሁም የተለያዩ ተደራሲያን ለተለያዩ ጉዳዮቻቸዉ በቀላሉ መዝዘዉ እንዲጠቀሙበት ይመች ዘንድ ነው፡፡

ትረካዉ አልፎ አልፎ በአጫጭር *ሰንኞች* የሚጀምረዉ ወይም የሚጨርሰዉ ነገር ለማጣፈጥ ያህል አልነበረም፡፡ ባለታሪኩ ዐውደ ዕለት ማሳታወሻዎቻቸዉ ላይ ያሰፈሯቸዉ ቁምነገሮች አብዛኛዎቹ *በዝርዉ* ከመጻፋቸዉ በስተቀር እንደ ቅኔ በሃሳብ የታመቁ ከመሆናቸዉ የተነሣ የገጣሚን መንፈስ መፈታተናቸዉ የወሰደዉ የአጻጻፍ ዘይቤ ነዉ፡፡ ማለትም *‹‹ግጠሙኝ ግጠሙኝ››* ይላሉ፡፡ አዘጋጁ በዚህ ፈተና ወድቋል፡፡ ስለሆነም ጥቂቶቹን የባለታሪኩን ሃሳቦች ከርክሞ ቤት ሠርቶላቸዋል፤ ዜማና ምት





አበጅቶላቸዋል፡፡ ለህትመት ካዘጋጃዉ መድብል ዉስጥም ከቷቸዋል፡፡

ይቺን ያህል ተፍጨርጭሮ ሲያበቃ የሕይወት ታሪክ መጽሐፍ ተደራሲያን የንባብ አምሮት ባይረካ ጉድለቱ የብርቅዬዉ ባላታሪክ ሳይሆን የአዘጋጁ ክህሎት ውስንነት መሆኑን በአክብሮት እገልፃለሁ፡፡ እንዲህ ተብሏልና፡-

> *‹‹ሕይወታቸዉን በደንብ መርተዉ ያለፉ ዓርዓያ ሰዎችን ማግኘት ብርቅ የሆነዉን ያህል በደንብ ተቀምሮ የተጻፈ የሕይወት ታሪክም ማግኘቱ ብርቅ ነዉ››፡፡ (ስኮትላንዳዊዉ ታሪክረ ጸሐፊ ቶማስ ካርቴል፣ 1795 - 1881)*

*ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን፡፡*

መልካም ንባብ

ወንድዬ ዓሊ

## አመሰግናለሁ

- *በዋጋ ሊተመኑ የማይችሉ የዶ/ር ብርሀኑ የሠላሳ ስድስት ዓመት ዐውደ ዕለታት ሰነዶችን በትውስት እረከብ ዘንድ የታመነ አድርገዉ ለቆጠሩኝ ሲስተር አልማዝ ታረቀኝንና ቤተሰቦቻቸዉን በቅድሚያ አመሰግናለሁ::*

- *በግልና በቡድን ቃለ ምልልሳዊ ዉይይት የተሳተፋችሁትን፣ ረቂቁን አንብባችሁ የሃሳብ ማበልጸጊያ አስተያየቶቻችሁን የለገሣችሁኝ ወገኖችንም እጅግ አመሰግናለሁ::*

- *ይህ መጽሐፍ የአሁኑን ቅርጽና ይዘት ይዞ እንዲወጣ የሕይወትና የአገልግሎት ታሪክ መጽሐፍ ዝግጅት የሥራ ቡድን አባላት ድርሻ ወደር አልነበረዉም፤ በእውነት አመሰግናለሁ!*

- *ከዕድሜዬ አጋማሽ በላይ በክርስቲያናዊ ሥነ ጽሑፍ፣ በታሪክ ጥናትና ምርምር የሥራ መስክ ላሳለፍኩት እኔ ግን የዶ/ር ብርሀኑን የሕይወት ታሪክ ለማዘጋጀት ዕድል የሰጠኝን ጌታ እግዚአብሔር ‹‹ክብርና ምስጋና ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ ይሁን›› ከማለት ወዲያ ከተለ ቤላ ምን እላለሁ!*





# 1. በመጀመሪያ - የፍፃሜዉን

ገና ድር . . . ድር ገና - በአዳም ወገብ ሰዉ ስትፈጥር፤
የምታወቀኝ ጌታ አምላኬ - ሳይሠፈር ዘመን በቁጥር፣
እነሆኝ እፊትህ አለሁ፣
ልቤን እፊትህ አፈሳለሁ፤
አንተ ሁሉን ቻይ አዋቂ! . . . እኔም የአምሳልህ ክፋይ፣
ለሰዉ ከቸርከዉ ዕድሜ . . . ሰባ ቢሆን ሰማኒያ፤
ከዚያም ያነሰ ብትሰጠኝ፣
ብቻ ፈቃድህ ይሁን... ከቁጥሩ ቀመር ምን አለኝ!?
ነገር ግን አንድ ልመና . . . እነሆኝ የእንባ ደብዳቤ፣
ከእዉቀትህ ጥቂት ልበደር፣ . . .
የእድሜየን ሰፍር እንድርጥ . . . የአንተን ራዕይ አንግቤ::

*(የአራት ዓይናዉ ጸሎት፡ ካልታተመ ጥራዝ)*

## *1.1. የቅርብ ሰዉ ቃል*

የሃያ አራት ዓመት ወጣት ሐኪም ሣለ ነው የተዋወቅሁት:: ለሠላሣ ሁለት ተከታታይ ዓመታት የቅርቡ - የልቡ ሰው - ሆኜ ቀይቻለሁ:: ከእግዚአብሔር አምላካችን በታች የእኔን ያህል ሊያውቀው የሚችል የለም ብዬ አምናለሁ:: ሠላሳ ሁለተኛው ዓመት ላይ በውል ልገነዘባቸው ያልቻልኳቸው አንዳንድ ለውጦች አይበት ጀመር:: ቢሆንም እንደ ቀድሞዬ ሁሉ በቀና አያሰብኳቸው በከፊልም ፈቃዱን ለመፈፀም ያህል አድርጊ የሚለኝን ብቻ አደርጋለሁ::

ብርሃኑ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ጊዜ አጥቶ አያውቅም:: ረጋ ብሎ ያስባል፣ ይጸልያል፣ ወደ ተግባር ይገባል. . .:: ሲከናወንለት

ያመሰግናል፤: እርምጃውን የሚገትት ነገር ሲያጋጥመው ሰብሰብ ብሎ ከአምላኩ ምሪት ይቀበላል።

በመጨረሻዎቹ ወራት ግን እንደ ኮንትራት ውል ሠራተኛ ከጊዜ ገደብ ጋር ውድድር የገጠመ ይመስል ነበር። ሁለንተናዉን የሰጠለት የእግዚአብሔር ሥራ እንደ ተገለጠለት ራዕይ መጠን ጉዳዮቹ በአግባቡ መከናወናቸዉን እንጂ ስለ ጊዜ ገደብ ደንታ አልነበረውም። ለመጨረሻዎቹ ቀናት ግን ለሱ ሆነና ብዙ ነገሮችን በጥድፊያ ያከናውን ነበር።

በዚህ ጥድፊያ ላይ እያለ ወደ አሜሪካ አብረን የምንጓዝበትን ሁኔታዎች አመቻቸ። እኔ ዝግጁ ስላልነበርኩና ጊዜዉም ስላልመሰለኝ ላለመሄድ አመንትቼ ነበር። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ያመለከተውን ነገር ሳያከናውን እንደ ማያርፍ ስለ ማውቅ እሺታዬን ነግሬዉ ለጉዞ መዘጋጀት ጀመርኩ። በመሠረቱ ብርሃኑን እንደ ልቤ የማገኘው ለሥራም ሆነ ለአገልግሎት እንዲህ ራቅ ብለን አብረን ስንጓዝ ነው። ስለሆነም በግሌ የጉዞ ዝግጁነት ቢጎድለኝም ከእርሱ ጋር መቆየትን እንደ ትልቅ ዕድል ነበር የቆጠርኩት። በዚያም ሆነ በዚህ ለመጋቢት 12 ቀን 1999 ዓም በረራ ዝግጅቴን ጀመርኩ።››

***

*በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ስለ መጨረሻዎቹ የሩጫ ቀናት የተረኩልን ሲስተር አልማዝ ታሪቀኝ ናቸው። ሲስተር አልማዝ የዶክተር ብርሃኑ ባለቤት ሲሆኑ ለሃያ አምስት ዓመት በትዳር አብረው ቆይተዋል፤ ሁለት ሴት ልጆችንም አፍርተዋል፤ እንቀጥል።*





## *1.2. የጉዞው ዋዜማ*

*ዋዜማው ለሲስተር አልማዝ የሚያባትሉ የሥራ ቀናት ነበሩ። ለጉዞ የሚሆኑ ዕቃዎችን መሸከፍ፣ ለዘመድ አዝማድ የሚሰጡ ገጸ በረከቶችን ማዘጋጀት፣ ባህር ማዶ የሚበተኑ ሰነዶችንና ሌሎች የህትመት ውጤቶችን ማደራጀት፤ ለልጆቻቸውና ለቀሪው የቤተሰብ አባላት የመኖሪያ ፍጆታ መሟላቱን ማረጋገጥ . . .ወዘተ። በአንድ ጊዜ የትዳር አጋር፣ የአገልግሎት ተጣማጅ፣ ሚስት፣ እናት ‹‹ለድሆች የምሥራች አገልግሎት›› ባለ ራዕይ መሆን የሚያስከትለውን ኃላፊነቶች ሁሉ መወጣት ነበረባቸው።*

*ለዶ/ር ብርሃኑ ደግሞ ዋዜማው ልዩ የአገልግሎት ውሎ ነበር። አገልግሎት የሰጡት ለክርስቲያን የጤና ባለሙያዎች ሕብረት ሲሆን ያስተማሩት ትምህርት ማዕከላዊ ይዘቱ ራዕይና ባለ ራዕይ የሚል ነበር። እግዚአብሔር የዕለቱን አገልግሎት ስለ ባረከላቸው እጅጉን የተደሰቱት ዶ/ር ብርሃኑ በዐውደ ዕለት ማስታወሻቸው ላይ የሚከተለውን አስፍረው ነበር።*

**የስኬቱና የመሰላሉ ምስጢር**

> *‹‹የተዋጣ አገልግሎት ነበር፤. . . (በመጨረሻ) እጅ ለእጅ ተያይዘን ጸለይን። መሪዎቹ ሲጸልዩልኝ መንፈስ እየወረደብኝ፦ ዕድሜውን እንደ ካሌብ አድርገው፣ ሲሉ አዳምጥ ነበር። ጸሎቱን ከጨረስን በኋላ አንድ ወንድም መጥቶ ኢያሱ 1፡1 - 9 ስለ አንተ ተሰጥቶኛል አለኝ።*
> *አንዲት እህት ግን የታጠፈ መሰላል በፊቴ መጥቶ ወደ ላይ ሲዘረጋ በራዕይ እያየች ነበር። ፍቺውም ‹እሱ ሲደክመው እኔ አሸጋግረዋለሁ› የሚል ነበር። ስለዚህ ሁሉ ጌታ የተባረከ ይሁን።*

**እንደ ካሌብ፡-**

*‹‹እናሸንፋለን፣ እንችላለን! የሚል የእምነት ሰው፤ እንውጣና እንውረስ!፡ እያለ የሕዝቡን ልብ የሚያፀና፣ ወርሶ ሌላውን የሚያወርስ ደግ ሰው፤ ከወጣትነት እስከ እርጅና፣ እስከ ሽምግልናም ሳይነዋወጥ የአገለገለ ሰው... ››*

**እንደ ኢያሱ፡-**

*‹‹የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማሻገር የተሰፋዋን ምድር ለማውረስ፣ ፅኑ ቃልኪዳን የጨበጠ ሰዉ . . .፤ (ዐውደ ዕለት 12/7/99)*

እንደዚህ ዓይነቱ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሚደረግ ጸሎትና የማጽናናት ቃል፡- ሳይጣል፣ ሳይተው፣ ሳይፈራና ሳይደነግጥ ሁለንተናውን በእግዚአብሔር ላይ ለጣለ ለማንኛዉም ሰው ትልቅ መንፈሳዊ መበረታታትን ያስታጥቃል። ዶ/ር ብርሃኑም በጉዟቸዉ ዋዜማ ሌሊቱን ያሳለፉት በዚህ ሁኔታ ነበር።

የሰነቁትንም የተስፋ ቃል መቼም ለሲስተር አልማዝ ሳያካፍሏቸው አልቀሩም። ለባላቤታቸዉም ሆነ በዐውደ ዕለት ማስታወሻቸው ሰፋ አርገው ያልገለፁት ግን በመሰላል ምሳሌ የተነገራቸውን ራዕይ ነው፤ በወቅቱ ለራሳቸውም ገና ደምቆ አልታያቸውምና። ምንም ያህል መንፈሣዊ ሰው ቢሆኑም እንኳን እንደ ማንኛውም ሥጋ ለባሽ ‹‹ሁሉን አወቅ›› ለመሆን ከቶም አይቻላቸውምና!! እንዲህ ባለ መንፈሣዊና ስሜታዊ አቋም ሆነዉ መጋቢት 12 ቀን 1999 ወደ አሜሪካ ተጓዙ።

***





እንደ ሚታወቀዉ በእያንዳንዱ የበረራ መተላለፊያዎች ተጓዦች ማሟላት የሚጠበቅባቸው ግዴታዎች አሉ። ፓስፖርትና ሌሎች ሰነዶች ማሳየት፣ ቪዛ ማስመታት፣ ዕቃ ማስፈተሽ፣ ዕቃ መቀበልና ማራገፍ፣ መልእክት መለዋወጥ፣ የተለመዱ ግዴታዎች ናቸዉ። ዶ/ር ብርሃኑ በዓለም ዙሪያ በተደጋጋሚና ለበርካታ ዓመታት የተጓዙ ስለሆነ በመተላለፊያ ጣቢያዎች የሚጠበቅባቸውን እነዚህን ኃላፊነቶች በሚገባ ያውቃሉ። የሲስተር አልማዝ ተሞክሮ ግን ይህን ያህል አልነበረም። አብረው በተጓዙባችው ቀደም ባሉ ዓመታት እነዚህን ሥራዎች ፊተኛ ሆነው የሚከውኑት ዶ/ር ብርሃኑ ነበሩ። በዚህ ጉዞ ላይ ግን ገሸሽ ብለው ይቆሙና ባለቤታቸውን ብቻቸውን እንዲያከናውኑ ይገፋፏቸዋል። ይህ ያልተለመደ ‹‹ቸልተኝነት›› ለሲስተር አልማዝ ግርታን ፈጠረባቸው።

‹‹ለምን እኔ!?. . .አንተ እያለህ?››

‹‹ከአሁን በኋላ የምትመጭው ብቻሽን ነው ፤ ሂደቱን መለማመድ አለብሽ።››

‹‹ካአንተ ጋር ካልሆነማ ብቻዬን አልመጣም፤. . .ብቻዬን?››

‹‹ለድሆች የምሥራች አገልግሎት ራዕይ ያንቺ ራዕይ ነው፤ አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአሜሪካም የፍትህ ሥርዓት ተመዝግቦ ሕጋዊ ዕውቅና አግኝቷል። ለወደፊትም በተደጋጋሚ መመላለስሽ አይቀርም። ባለ ራዕይ ራዕዩን በሰጠው ጌታው ላይ እንጂ በባሉ ወይም በሚስቱ ችሎታ ላይ አይደገፍም።››

ፍርጥም ባሉ ቃላትና ድምፀት አብራሩላቸው። በዚህን ጊዜ ሲስተር አልማዝ *«በቃ! ኤክሌሺያ ተነሺ አገልግሎቱ* ላይ የበለጠ ለማተኮር ሲል ይሆናል ይህን አገልግሎት ወደ እኔ ገፋ - ገፋ የሚያደርገው» አሉ እንጂ ከቶም ከዚህ ያለፈ ሌላ ምስጢር አልጠበቁም።

ሰው ሁሉ ነገሮችን የሚረዳበት አረዳድ *እንደ ሰብዕናዉ (እንደ ማንነቱ) ነው* ይባላል። ሲስተር አልማዝም የባለቤታቸዉን አገልግሎት በተመለከተ ‹ቀና - ቀናውን› ብቻ ለይቶ የሚረዳ ልቡና ያላቸው እመቤት ይመስላሉ። በባለቤታቸው ሕይወት ዉስጥ እየተከሰቱ የነበሩትን አንዳንድ እንግዳ ለዉጦች ሲመለከቱ የፍፃሜዉ መጀመሪያ መሆኑን ‹በእዉኔ ቀርቶ በህልሜም እንኳን ይመጣል ብዬ አልጠረጠርኩም› ሲሉ መደመጣቸዉ ለዚህ አባባል አንዱ ማስረጃ ነዉ።

***

ሁለቱ የሕይወትና የአገልግሎት ተጣማጆች በአሜሪካ ሁለት ወር የሚጠጋ ጊዜ አሳለፉ። በዋሽንግተን፣ ሳንፍራንሲስኮ፣ ላስቬጋስ፣ በልቲሞር፣ ኖርዝ ካሮላይና ተዘዋውረው ራዕያቸውን ለውጪ ወዳጆቻቸውና ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም ለኢትዮጵያ ክርስቲያን ማህበረሰብ አባላት አስተዋወቁ።

«የድሆች የምሥራች አገልግሎት» የሲስተር አልማዝ የረዥም ጊዜ ራዕይ ሲሆን ዶ/ር ብርሃኑ ደግሞ ራዕዩን ወደ ተግባር በመለወጡ ረገድ ከፍተኛውን ኃፊነት የወሰዱበት ወቅት ነበር (በምዕራፍ 13 ይብራራል)። ዶ/ር ብርሃኑ ከአምስት





ዓመታት በፊት ስለ ራዕዩ በዐውደ ዕለት ማስታወሻቸው ላይ የሚከተለውን መዝግበው ነበር።

> *«ነገሮች እንዴት ይገጣጠማሉ? ከታህሣሥ 1997 አንስቶ በውስጤ እያደገ የመጣ የምር ሃሳብ ነው። የተያዙት (ሌሎች የኤክሌሺያ ተነሺ) አገልግሎቶች እንደቀጠሉ፡*
>
> - *ድሆች ላይ አተኩሮ የሚሠራ አገልግሎት፣*
> - *ድሆችን፣ ለማኞችን ጭምር አምራች ዜጋ የሚያደርግ፣*
> - *በልማትና በመንፈሣዊ ሥራ ጣምራ ፈቃድ ያለው፣*
> - *ድሆችንና የአካባቢ ሰዎች የምታገለግል በድል የምትገሠግስ ቤተ ክርስቲያን የሚተክል፣*
> - *ዓለም አቀፍ ግንኙነት የሚፈጥር አንድ አገልግሎት በአስቸኳይ ተግባራዊ ማድረግ አለብን።*
> - *የሚገርመዉ ነገር እኔ የውጪ ጉዞዎችን (ሁኔታዎችን) እንደማመቻችና የዓለም አቀፍ ቢሮዉም በሳን ፍራንሲስኮ እንደ ሚከፍት . . . አልማዝ ቀደም ብላ ራዕይ አይታ ነበር። (ዐውደ ዕለት የካቲት 16 ቀን 1997)*

እንግዲህ ይህንን ያህል ግዙፍ ዓላማና ግብ የፀነሰ አገልግሎት በሁለት እግሩ ለማቆም ነበር ሁለቱ አገልጋዮች ወደ አሜሪካ የተጓዙት። አገልግሎቱን በተመለከተ የተዘጋጀዉ ምክረ ሃሳብ (ፕሮፖዛል) እና ሌሎች ሰነዶች እንደሚያመለክቱት ይህ ራዕይ እዉን ሆኖ ወደ መርኃ ግብር (ፕሮጀክት) ሲለወጥ ለሕንፃ ግንባታ ብቻ 23 ሚሊዮን ያህል ብር የሚያስፈልገው የአገልግሎት ተቋም ነው።

አንዳንድ ሰዎች የገንዘቡ መጠን ሲነገራቸው እንደ መደንገጥ ይዳዳቸው ነበር። ይህንን የተገነዘቡት ሲስተር አልማዝ በተጓዙባቸዉ አካባቢዎች ስለ ራዕዩ ይዘት ከአብራሩ በኋላ

የገንዘቡን መጠን በትህትና እንኳን ለመናገር ሙሉ ነፃነት አይሰማቸውም። ዶ/ር ብርሃኑ ደግሞ ያላዩ መስለው የአልማዝን ሁኔታ ይከታተሉ። አንድ ቀን ታዲያ እንዲህ ሆነ፡፡፡ ሚሊዋኪ በተባለች ቤተ ክርስቲያን የራዕይ ገለፃ ካደረጉ በኋላ ገንዘቡ ላይ ሲደርሱ ሳቅ ብለው በለሆሳስ ድምፀት ‹‹ይህን ያህል ሚሊዮን ይወስዳል ብለን እናስባለን›› ሲሉ ተናገሩ። ለወዲያው አንድ ነገር በውስጣቸው አለፈ። ዶክተሩ በዕለት ማስታወሻቸዉ መዝግበውታል፤

> *‹‹ጥሩ ጊዜ ነበረን። . . . እኔ ‹ዋናው ጥሪያችን› በሚል ርዕስ የሁለት ክፍለ ጊዜ ትምህርት አቀረብኩ። . . . የተባረከ የአገልሎት ቀን ነበረ። አብረንም የራዕይ ገለፃ አደረግን።*
>
> *በእረፍት ጊዜ አልማዝ ከእህቶች ጋር ስትነጋገር ስለ በጀቱ ስትናገር ሣቅ አለች። ወዲያውም የሣራን ታሪክ የሚያስታውስ ድምፅ ወደ እርሷ መጣ፤ ደነገጠችም። ሣራ ብትስቅም ይስሐቅ እንደ ተወለደ ሁሉ እርሷም የተቀበለችው ራዕይ ተግባራዊ እንደሚሆን አመነች። ታማኙ አምላኬ ያደርገዋልና ስሙ የተባረከ ይሁን። አሜን!! (ዐውደ ዕለት 14/8/99)*


ባለ ራዕዮቹ እንዲህ እርስ በርሳቸውና ከአምላካቸው ጋር ቅርብ ሆነው አሳለፉ - በአሜሪካ። የአማርኛ ተናጋሪዎች እክሌ እኮ ሁልጊዜ ደስተኛ ነች ለማለት ሁሌ ‹‹ፋሲካ ነች›› እንደ ሚሉት ዓይነት ቆይታዉ ለሲስተር አልማዝ ፋሲካ ሆኖላቸው ከረመ። ግን ቤርሳቤህና ጽኒኤል የሌሉበት ደስታ ጎዶሎ ሆነባቸው፤ እናም አሉ፡-

> *‹‹እኔ ከባለቤቴ ጋር በእርጋታ ያጣጣምኳቸው እነዚህን የመሰሉ ቀናት ለልጆቻችንም ቢደርሳቸው እንዴት መልካም በሆነላቸው! ብዬ ተመኘሁ። . . . ልጆቻችን እኮ አባታቸውን ጠግበውት አያውቁም፤ እንዲሁ እንደራባቸው ትዳር ይዘው ከቤታችን ከወጡ ዳግመኛ የእኛ አይሆኑም፤ የባሎቻቸውና የልጆቻቸው እንጂ። ስለሆነም ከአዲስ አበባ ወጣ ብለን ቢቻል ወደ ውጪ አገር ወጥተን የቤተሰብ የፅሞና ጊዜ መውሰድ እንዳለብን ማማከር አለብኝ።*
>
> *በጉዳዩ ተስማማንበትና ከወራት በኋላ ሐምሌ ወይም ከሰኔ ወር 1999 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት ሳምንታት ያህል ከልጆቻችን ጋር ለማሳለፍ ወሰንን። ይህንንም ለልጆቻችን አስታወቅናቸው። በሕይወታቸው ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ ያልሆነ ገራገር የቤተሰብ ጊዜ የሚያሳልፉበትን ቀናት በናፍቆት ሲጠባበቁ ሰነበቱ።››*

## 1.3. ሰዓቱ ደረሰ

የተወሰነው ጊዜ ደረሰ። የጽኒኤልና የቤርሳቤህ ልብ ቆመ። ጽኒኤል ከአባቷ ጋር ጠንካራ ሃሳቦችን ማንሣትና መወያየት ትወዳለች - ለምዳለችም። የቤርሳቤህ ዝንባሌ ከዚህ በተቃራኒዉ ጫፍ የቆመ ይመስላል። ከረቂቅ ሃሳቦች ጋር መታገል አይሆንላትም። ገፍቶ ከመጣባትም ዘወር ብላ ታሳልፈዋለች። ‹መጨናነቅ› አትወድም።

ሰባኪ፣ አስተማሪ፣ ባለ ራዕይ፣ የብዙ ቦርዶችና ኮሚቴዎች አባል/መሪ፣ሽማግሌ፣ አስታራቂ፣ አማካሪ... እዚህ ስብሰባ፣ እዚያም ስብሰባ፤ እዚህ አገልግሎት፣ እዚያም አገልግሎት ውሎ የሚመጣ አባት የልጆቹን ሙሉ ፍላጎት ለመመለስ እንዴት ጊዜ ሊኖረው ይችላል? አሁን ግን ለእረፍት የተቀጠረው ጊዜ ስለ ደረሰላቸው ደስ አላቸዉ።



*የዶ/ር ብርሃኑ ነፍስ ግን በጊዜ አጣብቂኝ ውስጥ ዉስጥ ወድቃ እየተጨመቀች መሆኑን ማን በነገራቸዉ? ቀጭን መለኮታዊ ትዕዛዝ መጥቶባቸው (ወይ መጥቶላቸው) ሁለንተናቸውን ውጦባቸው ነበርና!*

ዶ/ር ብርሃኑ እንግዲህ በአባትነትና በእግዚአብሔር ባርያነት መካከል ያለውን መሳሳብ አልፈዉ መወሰን ሊገባቸዉ ነዉ። ነገር ግን የማንን ፈቃድ ለመፈጸም ቅድሚያ ይሰጡ ይሆን?! ያለ ምንም መገደብ (ይሉኝታ) የልባቸውን አውጥተው በሚዘረግፉበት የዐውደ ዕለት ማስታወሻቸዉ እንዲህ ብለው አሠፈሩ፡-

> *‹‹የሰው ልጅ የሚከብርበት ሰዓቱ ደርሷል (ዮሐ12፡23 - 28) ይህ ጊዜ ለእኔ መሰስተኛ ሞት ነው (የሚሆነው) ውኃ ብቻ*





> *እየጠጣሁ መጸም (መጸለይ) እንዳለብኝ ገባኝ። ጌታ እንደዚህ ነበር የጸመው።. . .አሜን ሃሌሉያ!!›› (ዐውደ ዕለት 7/9/99)*
> *‹‹ይህ ጊዜ (ጾምና ጸሎት ለመውሰድ) የተገለጠው በ30/3/99 ነበር።. . . ሙሴ እንደ ሆነለት በእግዚአብሔር ሕልዎት መሞላት እንደሚያስፈልገኝ ተረዳሁ። ጉዳዩን ሳሰላስል የሠላሳ ቀናት ጾም እንዳደርግ የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ሰማሁ። የሰው ልጅ የሚከብርበት ቀን ደርሷል የሚለው ቃል (የጾምና ጸሎት) የፕሮግራሙ ማዕከላዊ ሃሳብ እና ርዕስ ሆኖ ጸና!*
>
> *ስለሆነም ይህን ፕሮግራም በጉጉት ነው የጠበቅሁት፤ በእግዚአብሔር ክብር ተሞልቼ (blasted) ሆኜ ዘመኔን በድል በምጨርስበት ሙላት ውስጥ እገኝ ዘንድ።›› (ዐውደ ዕለት 26/9/99)*

የዶ/ር ብርሃኑ የአገልጋይ ባሪያነት - ከሥነ ሕይወታዊው የአባትነት ኃላፊነት በለጠና በቅድሚያ ለመንፈስ ቅዱስ ትዕዛዝ መሸነፍን መረጡ፤ እናም ሰኔ 4 ቀን 1999 ዓ.ም ለሠላሳ ቀናት ሊቆይ ያለዉን የጾምና የጸሎት ጊዜ ጀመሩ። ጽኒኤል *‹‹ኧረ ባቢ! ሳልጠፋ ቀን ለእረፍት በመረጥናቸው ቀናት ለመጾም ለምን መረጥህ?››* አለች፤ በልጅነት መብቷ በማጉመትመት። ሲስተር አልማዝ ደግሞ አሁንም ሌላ የራሳቸዉን ቅን ግምት ሰነዘሩ።

> *‹‹እግዚአብሔር በአገልግሎታችን ፊት የተደቀኑትን ችግሮች ያስወግድልን ዘንድ ነው የሚጸመው፤ ባይሆን ቀን ቀን እንኳን እየጾምኩ ከጎኑ መቆም አለብኝ - ሲሉ።*

ዶ/ር ብርሃኑ ከጾምና ጸሎት ጎን ለጎን አንዳንድ ወሳኝ አገልግሎቶችንና የቤት ሥራዎችን ማከናወን ነበረባቸው። አልፎ አልፎ አዋዋላቸውን ይመዘግቡ ነበር።



*‹‹ያህዌ ይርዔ በዚህ ዕለት የመጀመሪያውን የኤክሌሺያ ተነሺ ቢሮ ተከራይተን ዕቃ አስገባን። ሁሉን ጨርሰን ልንወጣ ስንል. . . ተሰባስብን ጸለይን። ጌታ ሆይ ስምህን እንጠራለን ብዬ ስጀምር ያህዌ ይርዔ የሚለው ስም በድንገት ወደ እኔ መጣና ይህን ስም ጠራሁ። . . .ጌታ በአገልግሎታችን ላይ ረድዔቱን ተዓምራቱን ይቀጥላል። ያህዌ ይርዔ እግዚአብሔር ያዘጋጃል። (ዐውደ ዕለት 6/10/99)*

‹‹የኤክሌሺያ ተነሺ›› የባለ አደራ ቦርድ ስብሰባንም የተካፈሉት በጾምና ጸሎት ቆይታቸው ወቅት ነበር። ቦርዱ ከተነጋገረባቸው አጀንዳዎች አንዱ ለአገልጋዮቹ ስለ ሚቆረጠው ቀለብ ነበር። ዶ/ር ብርሃኑ በአገልግሎቱ አስተባባሪነታቸው የተቆረጠላቸው ቀለብ ሲነገራቸው ሰሚውን ያስደመመ ምላሽ ሰጡ።

*‹‹ይኼ ሁሉ ምን ያደርግልኛል? . . . ባይሆን ይህንን ያህል ቀንሱና ቁረጡልኝ›› የሚል።*

ሲስተር አልማዝ ዝርዝር ጉዳዩን ባይረዱትም ባለቤታቸዉ ይህን ‹ቀለቤን ቀንሱልኝ› ማመልከቻ ለቦርዱ ለመናገር የሚያበቃቸዉን የዉሳኔ ሃሳብ ለመድረስ የሦስት ወራት የቤት ሥራ ለቤተሰቡ በተለይም ለእሳቸዉ ሰጥተዋቸዉ እንደ ነበረ ያስታዉሳሉ። የቤት ሥራዉም ስኳርና ጨዉ ሳይቀር የየወሩን አስቤዛ በጥንቃቄ መመዝገብ ነበር። እንግዲህ ቦርዱ ሊሰፍርላቸዉ ያሰበዉ ቀለብ ከሦስቱ ወር አስቤዛ አማካኝ ወጪ በላይ ሆኖ መገኘቱ ከብዷቸዉ ነበር ከዕለት እንጀራዬ በላይ ምን ያደርግልኛል? ለማለት ያበቃቸዉ። ይህንን በተመለከተ፡-





*‹‹ምን ዓይነት መሰጠት ነው?! ... የሙሉ ጊዜ አገልጋይነት እንደ ተዘዋሪ የማትርፊያ (ጥቅም የማስገኛ) ዘዴ በተቆጠረበት ዘመን ድሆችን ለማገልገል በገዛ ፈቃዱ የድህነት ኑሮን ለመኖር ከጨከነ ሰው ጋር መስራት መታደል ነው።›› አንድ የቦርድ አባል የተናገሩት ነበር።*

የኑሮ ውድነት ጣሪያ በነካበት ወቅት፣ ትምህርታቸውን ጨርሰው ሥራ ፍለጋ ላይ ያሉ ሁለት ልጃገረዶች እያስተዳደሩ፡- ‹‹ይኼ ይበቃኛል፤ ይህንን ቀንሱልኝ›› ማለትን ለሰሙ ሁሉ በዚያ ሰሞን ፈፅሞ ራስን መካድ የሚጠይቅ የፅናት ምሳሌ ሆኖ ሰነበተ። ወደ ጾም ጸሎቱ እንመለስ።

ጾምና ጸሎት መውሰድ ለዶክተር ብርሃኑ መንፈሳዊ ሙላትን የሚለማመዱበት የሕይወት ዘይቤአቸው አንዱና ዋናው ክፍል ነው። እንዲህ እንደ አሁኑ በልዩ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሲመጣላቸዉ ብቻ ሳይሆን በማንኛውም *ሁኔታ፣ ቀንና ሰዓት* ለልባቸዉ ሲሰማቸው ጾምና ጸሎት ይወስዳሉ። ከሠላሳ ሦስት ዓመታት በፊት በያዙት የዐውደ ዕለት ማስታወሻ፡- *‹‹ወደ ጌታ መቅረብ እንዳለብኝ ተሰማኝና ራት ሳለመብላት ወስኜ ለጸሎት ተንበረከክሁ››* ሲሉ መዝግበውታል።

ይህ ከቁርስ ወይም ከምሳ በኋላ አንስቶ ጾም የመዉሰድ ነገር አብዛኛው ምዕመን ከሚያውቀው ጾም ለየት ያለ ልምምድ መሆኑ ነው። ጾምና ጸሎት ሲወስዱም ዝርዝር የጸሎት ርዕሶችን ይመዘግባሉ። ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸውን መልስ ደግሞ በሠንጠረዥ (ቻርት) መሰል - አጻጻፍ በየአንፃሩ ይመዘግባሉ። የዚህኛው ጾም ቆይታ ግን በአብዛኛው ድፍን ያለ ነው።

አልፎ አልፎ ግን ‹‹የሰዓቱን›› ነገር የሚያመላክቱ አገላለጾችና ሃሳቦች በዐውደ ዕለት ማስታወሻቸው በጥንቃቄ ተመዝግበዋል፡፡ ጥቂቶችን እነሆ፡-

**በ21ኛው ቀን**

*‹‹ማታ ለመተኛት አልጋ ላይ ሆነን ሳለን (ከአልማዝ ጋር) ስላለሁበት ሁኔታ ተነጋገርን፡፡ በጾም 21 ቀን ቆይቻለሁ፡፡ ጉሮሮዬን የሚሞላው ሃክታና የአፍ ጣዕም መለወጥ ብቻ ነው ዋናው የሚያስቸግረኝ፡፡ ወዲያውኑ ጌታ ያሳለፈውን የጾም ጊዜ አሰብሁ፤ ጌታ፡-*

- *በቤት ሳይሆን በምድረ በዳ፣*
- *በስፖንጅ መንበርከኪያ ሳይሆን በደረቅ መሬት ላይ፣*
- *ንጹሕ ውኃም አያገኝም ነበር፤ የውሃንም ሙቀት መቆጣጠር (ማቀዝቀዝ) አይችልም ነበር፡፡*

*ይህን ሳስብ ለሰው ልጆች ብሎ የገባበት መከራ ተሰማኝና ዕምባ እያፈሰስሁ፤ መከራው አንጀቴን በላው. . .፡፡ (ዐውደ ዕለት 24/10/99)*

**የኤሎሄ ሳምንት**

*የእግዚአብሔርን ልዩ ጉብኝት በመጠበቅ ሳሉን ብቻዬን ነበርኩ፡፡ የሚገርመው ነገር ጌታ የፈተና ሳምንት እንዲሆን ፈቀደ፡፡ ርዢ ቦታ እያቀያየረ ያመኝ ነበር፡፡ መናፍስት በሕልምና በተለያየ መልኩ ያውኩኝ ነበር፡፡.... (በተለይም) የሞት መናፍስት፡፡ ከሚልኪያስ ጋር በሕልሜ ጊዜ ወሰድሁ፡፡ ከሚልኪያስ (ዶ/ር ሚልኪያስ ቀደም ብለው የአረፉ የዶ/ር ብርሃኑ የረዥም ጊዜ የልብ ጓደኛ ነበሩ) የተለያዩ አደጋዎች አሳፋሪ ትእይንቶች (አየሁ)፡፡ እንዲሁም በአካልም በስሜትም ግርግርታ የሚፈጥሩ መናፍስት (ይታገሉኛል)፡፡ ስገሥፃቸውም አለመሄዳቸው ጌታ እንደፈቀደላቸው ያመለክታል፡፡. . .*





*በአጠቃላይ ኤሎሄ፣ ኤሎሄ ላማሰብቅታኒ ይመስላል፡፡ (የጾሙ መጨረሻው ሳምንት ዐውደ ዕለት)*

## *1.4. ጽኒኤል በኤሎሄዉ ሳምንት*

የጾምና የጸሎት ፕሮግራማቸዉን ለማጠናቀቅ አንድ ሳምንት ሲቀራቸዉ ፍራሽ ሳሎን እንዲነጠፍላቸው ጠየቁ፡፡ ቤርሣቤህና እናቷ እየተረዳዱ ሲያዘጋጁ ጽንኤል በአባቷ ትይዩ ተቀምጣ ፊታቸውን ታነብ ነበር፡፡ ከሦስት ሳምንት በላይ ያለ ምግብ የሰነበተ አልመስል አላት፤ እንዲያውም ገጽታቸዉ *የሆነ የደስታ ፀዳል* ረብቦበታል፡፡ እርግጥ ነው ይህ ሳምንት *ለሠላሳ ስድስት ዓመታት* በዐውደ ዕለት የመዘገቧቸውን ማስታወሻዎች ዝርዝር ማውጫ (Index) አዘጋጅተው የጨረሱበት ሳምንት ነው፡፡ ስለ ተከናወነላቸውም የተሰማቸውን እርካታ ለሲስተር አልማዝ ተናግረዋል፡፡ በፊታቸው ላይ የሚነበበው ሐሴት ግን ከዚህ የላቀ ሆነባትና፡-

*‹‹ባቢ ዛሬ በልዩ ሁኔታ ደስ ያለህ ትመስላለህ››* አለች ጽንኤል፡፡

‹‹አዎ! በጣም ደስ ብሎኛል፤ እግዚአብሔር ጸሎቴን ሰምቷልና፡፡››

*‹‹በምን ርዕስ ነበር የምትጸልየው - ባቢ?››*

መልሱን ከመናገራቸው በፊት እነ ቤርሳቤህ *ሥራቸውን* አጠናቀው ሊመለሱባቸዉ ሆነ፤ ሊነግሯት ያለዉን ምስጢር አንጠልጥለዉ ተዉትና፡-

‹‹ጽንዬ ፕሮግራሙን ስጨርስ ነው የምነግርሽ፣ እሺ ጽንዬ! . . . እሺ!››

ሲስተር አልማዝ የኤሎሄውን ሣምንት አሁንም ደግ ደጉን ብቻ እያሰቡ ነው ያሳለፉት:: በዶ/ር ብርሃኑ ገጽታ ላይ የሚነበበዉ ደስታ የመከናወን ውጤት እንደሆነ አድርገዉ ነበር የተረጎሙት:: ‹‹ጌታ ስለረዳው ረክቶ ነው›› አሉ ለራሳቸዉ:: ነገር ግን ገጽታቸዉ ላይ የሚነበብባቸው ደስታ በዶ/ር ብርሃኑ ሕይወት ውስጥ እያለፈ ከነበረው ኣሎሄ በተቃራኒ መሆኑ አሁን - አሁን ቤተሰቡን እያስገረመ የመጣ ነገር ነው:: ሲስተር አልማዝ ይህንን መገረማቸውን ያጠቃለሉት እንዲህ በማለት ነበር :-

> *‹‹አሁን ላይ ሆኜ እንደ ገና ሳስበው ለመሆኑ ይህንን ሁሉ ዓመታት የኖርኩት እንደ እኔ ሥጋ ከለበሰ ሰው ጋር ነበርን? እላለሁ::››*

ሐምሌ 4 ቀን 1999 ዓም ሰላሣኛውን ቀን ደፈኑ፤ በማለዳ ተነሥተው ጸለዩ:: በተለዬ የፊደላት አቀማመጥና በደማቅ የብዕር ቀለም የሚከተለው ማስታወሻ በዐውደ ዕለታቸው ላይ አሠፈሩ::

> *የሠላሣ ቀን ጾም ተገባደደ!! ጌታ እግዚአብሔር ይንን ስላስቻለኝ እጅግ አባርከዋለሁ!! እውነት አይመስልም፤ ግን እውነት ነው! ሃሌሉያ! አሜን::›› (ዐውደ ዕለት 4/11/99)*

ከሰዓት በኋላ የመደምደሚያ ጸሎታቸውን ይዘት ደግሞ እንደሚከተለው መዘገቡ::

> *‹‹በዚህ ዕለት የወሩን ቆይታ መደምደሚያ ፀሎት በእምነት ጸለይሁ:: የጸሎቴ ማዕከላዊ የተስፋ ቃል የሰው ልጅ ይከበር ዘንድ ሰዓቱ ደርሷል የሚለው ነው::›› (ዐውደ ዕለት 4/11/99)*





## *1.5. በሱባዔው ማግሥት*

የሠላሳው ቀን የጾምና ጸሎት ተፈጸመ:: በዶ/ር ብርሃኑ ውስጥ የሚያልፈው ኣሎሄ ግን እንዳልተቋረጠ ደፍሮ መናገር ይቻላል:: ምስጢሩን የሚያውቁት እሳቸውና እግዚአብሔር ብቻ ናቸዉ:: ለቀሪዎቻችን የተዉልን ማስታወሻ እንዲህ ይላል:-

> *‹‹ከ31ኛ እስከ 33ኛው ቀን ድረስ በሞት ሸለቆ ውስጥ (ከረምኩ)::›› (ዐውደ ዕለት 8/11/99)*

35ኛው ቀን ላይ ደመናዉ ፈገግ አለ:-

> *‹‹ስፔሺያል (ልዩ) ምህረት. . . እግዚአብሔር እኮ በልዩ መንገድ ክብሩንና ስሙን ገለጠ! (ዐውደ ዕለት 10/11/99)*

በተከታታዮቹ ቀናት ወደ የተለመደው የአገልግሎት ሩጫቸው ገቡ:: እንግሊዝ፣ ማሊ፣ ታንዛኒያ፣ ሲንጋፖር ሄደው አገለገሉ፤ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ተካፈሉ:: ሲንጋፖር የተጓዙት ከሲስተር አልማዝ ጋር ነበር:: እንደ አለፈው የአሜሪካ ጉዞአቸው ሁሉ ውጣ ውረዱን ለባለቤታቸው ተዉላቸው:: ለምን?! አሉ ባለቤታቸዉ::

> *‹‹ነገርኩሽ እኮ! ከአሁን በኋላ ውጣ ውረዱን ሁሉ ብቻሽን ነው የምትጋፈጪው፤ ብትላመጅው ይሻልሻል::›› አጭር - ቀጭን መልስ::*

***

በለንደን፣ በታንዛኒያና በማሊ ቆይታቸው ጊዜ በሚመጡት ጥቂት ወራት ተመልሰዉ እንዲመጡ የተለያዩ የአገልግሎት ግብዣዎች ቀርበውላቸው ነበር:: አንዱንም ግብዣ አልተቀበሉም:: በታንዛኒያ ላለችዉ ቤተክርስቲያን የሁለት ቀን

ሥልጠና ከሰጡ በኋላ ግን በዚያ ለሚገኙት ሁለት የቤተክርስቲያን መሪዎች ስለ ‹‹*ሰዓቱ ደረሰ*›› ምስጢር ትንሽ ፍንጭ የሚያመላክት ምላሽ ሰጥተዋቸዉ ነበር።

> *‹‹ከአሁን በኋላ አልመለስም፤ ጊዜ የለኝም ጊዜዬን ጨርሻሁ፤ ጌታ አገልግሎትህን የሚረከቡ ተተኪዎች አዘጋጅ ብሎኛል!›› የሚል።*

## *1.6. ‹‹ጊዜ የለኝም!››*








ጵንኤል ብርሃኑ ‹ጠያቂ› ነች። ይህንንም ባህርይዋን አባቷ እንደ ሚወዱላት ታውቃለች። እሳቸዉም ጥያቄዎቿን ለመመለስ ታክተዉ አያውቅም። በሠላሳዎቹ ቀናት የመጨረሻ ሳምንት ላይ ለጠየቀቻቸው ጥያቄ መልሱን ለመንገር ቀጠሮ የያዙላት ቢሆንም ጥያቄዋን እንደገና ለማንሣት የተመቻቸ ጊዜ ሊፈጥሩላት አልወደዱም ነበር፤ ባልተለመደ ሁኔታ ጊዜ ነሷት። ተጨማሪ ሦስት ወራት አለፉ።

እርግጥ ነው፣ ከሐምሌ 1999 አጋማሽ አንስቶ በአባቷ የዕለት በዕለት ሕይወት ላይ ጉልህ ለውጦችን ትመለከት ነበር። የጸሎት ጊዜያቸው ተራዝሟል፣ አገልግሎት ለመስጠት የሚዘጋጁባቸው ጊዜያት ከወትሮዉ ይልቅ ሰፋ ብለዋል። እንደገና ለማሰናዳትና ለማደራጀት ምቹ ሁኔታ ሲጠባበቁላቸው የነበሩትን የማስተማሪያ መጻሕፍት፣ ማኑዋሎች (መምሪያዎች)፣ የጥናት ጽሑፎች ምክረ ሐሳቦች (ፕሮፖዛሎች) እንደ አዲስ ማቀናጀት ጀምረዋል። ፋታ አልነበራቸውም። ስለሆነም ቀድሞም ቢሆን በቂ ያልነበረውን የእንቅልፍ ሰዓታቸውን ቆንጥረው - ቆንጥረው ወደ አራት ሰዓት ብቻ አወረዱት።

ሰዉ ምንም ያህል ትጉ ቢሆን ‹‹*ውስንነትን*›› ያህል ገደብ እግዚአብሔር ጥሎበታልና ዶ/ር ብርሃኑም ከዚህ ገደብ ነፃ አልነበሩም። ስለሆነም የኤክሌሺያ ተነሽ እና ሰድሆች የምስራች አገልግሎቶች ልዩ ልዩ ኃላፊነቶችን ወደ ሲስተር አልማዝ ገፋ ማድረግ ጀመሩ። የሲስተሯ ግርታ ጨመረ።



*‹‹አሁን ከሆንኩት በላይ ለመሆን አቅሜ፣ ችሎታዬ፣ ጤንነቴና በቤተሰብ ውስጥ ያለብኝ ኃላፊነት ይፈቅዳል!?. . . ጌታ ሆይ ጉልበት ሁነኝ፤›› ከማለት በስተቀር ምርጫ* አልነበራቸዉም፡፡

## *1.7. የመጨረሻዎቹ ቀናት*

**በማቱሳላ ምሣሌ - የዓመታት ክምር ተራራ፣**
**ቀለሙ በደበዘዘ - በማይደምቅ በማይብራራ፤**
**ድምበር ሳያዉቁ - መደንበር፣**
**እልሻም እንደዚያስ - ልኖር!**
**ዕድሜዬን እንደ ባረከዉ - በምሪት መሸተ በነጋ፣**
**ሕይወቴን በዕዉቀት እንደኖርኩ - በዕዉቀት ሰብስበኝ አንተ - ጋ'፡፡**

**(ከአራት ዓይናዉ . . . የቀጠለ)**

ዶ/ር ብርሃኑ የዕድሜ ጀንበራቸዉ ሳትጠልቅ በፊት ሁሉን በጥድፊያ ማከናወን እንጂ ‹‹ፀሐይን ባለችበት የማቆም›› ኃይልና ፈቃድ እንዳልተሰጣቸዉ ይገነዘባሉ፡፡ ይመሻል - ይነጋል፤ ይነጋልም - ይመሻል፡፡ ‹‹የሰዓቱ ደረሰ›› ምስጢራት ሊገለጹ ሃያ ቀናት ያህል ቀሩ፡፡ እነዚያ ሰሞናት የዶ/ር ብርሃኑ የዐውደ ዕለት ማስታወሻ በብዕራቸዉ ሳይቀልም - ሳይወዛ የከረመበት ሰሞናት ናቸዉ፡፡ በዚያዉ ሰሞን ጽንኤልና አባቷ አንድ የጸሎት ፕሮግራም ተካፈሉ፡፡ እሱ የሚባሉ የጸሎት ሰዎች የተካፈሉበት ጉባዔ ነበር፡፡ በመካከል አንዲት የጸሎት አገልጋይ ጽንኤልና አባቷ ወደ ተንበረከኩበት መጣችና በመገለጥ የተቀበለችውን መልእክት ለአባቷ ስታስተላልፍ ጽንኤል ጆሮዋን አቁማ አዳመጠች፡፡

*‹‹ጸሎትህን አድምጫለሁ፤ ክብሬን አሳይሃለሁ ጊዜውም እነሆ ደርሷል፤››*

አለች - መልእክተኛዋ፡፡





*‹‹አሜን! ጌታ ሆይ እንደ ፈቃድህ ይሁንልኝ››*

ሲሉ ምላሽ ሰጡ፤ በጸሎት መንፈስ በተሞላ ቃና፡፡

ከጸሎት በኋላ ወደ ቤታቸው እየሄዱ ሳለ ጽንኤል ከአምስት ወራት በላይ በልቧ ገብቶ ያብሰለሰላትን ጥያቄ አነሳች፤ እንዲህ ስትል፡-

***‹‹ባቢ መልእክቱ ከእግዚአብሔር ነው ብለህ ተቀበልከው? . . . መንፈስ ቅዱስ መሰከረልህ?››***

‹‹አዎ! እግዚአብሔር ይባርካት፤ ጌታ በእሷ በኩል ያረጋገጠልኝ መልእክት ነው፡፡››

***‹‹እንዲህ ያለ ጸሎት ትጸልይ ነበር እንዴ?››***

‹‹አዎ! የሠላሳው ቀን የጾም ጸሎት ማዕከላዊ ነጥብ እኮ የሰው ልጅ የሚከብርበት ሰዓቱ ደርሷል የሚል ነበር፡፡››

***‹‹ግን. . . የእግዚአብሔርን ክብር አይቶ ማንም በሕይወት አይኖርም ብሎት የለ - ሙሴን?››***

‹‹እንደ ሙሴ ሳይሆን እንደ ክርስቶስ መክበር››

***‹‹. . .ማለት. . . ወደ እግዚአብሔር አብ መሄድ? (ሞትን መሞት ላለማለት)››***

‹‹አዎ! ልሄድ ከጌታ ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፤››

***‹‹አይ ባቢ!. . .አንተ ደግሞ ታበዛዋለህ!››***

‹‹ይህን ጉዳይ ለማንም እንዳትናገሪ! እሺ ጽኒዬ!››

እነዚህን ቀናት ወደ ኋላ እያስታወሰች ጽንኤል ስትናገር፡- *‹‹በዚያን ሰሞን እኮ ባቢ በአካል እንጂ በመንፈሱና በልቡ ከእኛ ጋር አልነበረም፤ . . . በምድርና በሰማይ መካከል የተንሣፈፈ ዓይነት ይመስለኝ ነበር›› ብላለች፡፡*

***

ቀናቱ ቁልቁል ሲቆጠሩ ከ72 ሰዓታት በታች ቀርተዉ ነበር። በጢራኖስ የደቀ መዝሙርነት ትምህርት ቤት ሲያስተምሩ ውለዉና አምሽተው ነበር ወደ ቤታቸው የገቡት። ሳሎን ሶፋዉ ላይ አረፍ ከማለታቸዉ ርሂያቸው የፈጠረባቸውን የህመም ስሜት ለማስታገሥ እግራቸውን ጠረጴዛው ላይ ሰቀሉት። ጵንኤል ጠጋ ብላ እየደባበሰችላቸዉ፡-

> *‹‹ባቢ ይኼ ነገር እኮ እብጠቱ ጨመረ፤ አንተ ደግሞ አትጠነቀቅለት ነገር. . .››* አለች፡፡
>
> ‹‹አይዞሽ ጵኒዬ ወይ ከኔ ላይ ይነቀላል ወይንም እኔ ተነቅዬ ወደ አባቴ እሄዳለሁ፡፡››
>
> *‹‹ባቢ! እንግዲህ ጀመርክ፤ የምን መነቀል ነው?*
> *. . . መንቀል እንጂ!››*

ውይይታቸዉ ከዚህ በላይ ሊገፋ አልቻለም። የቀን ቁጥር ግን ቁልቁል መጣደፉን ተያይዞታል።

## *1.8. የካቲት 7: ዜሮ - ሰዓት*

አሮጌ መኪናቸውን አስነስተው ወደ ቡታጅራ መንገድ ጉዞ ቀጠሉ። ሲስተር አልማዝ ባለቤታቸዉ ብቻቸውን እንዲጓዙ ልባቸው አልፈቀደም፤ አብረው እንዲሄዱም ጠይቀዋቸው ነበር። በአዲስ አበባው የአገልግሎት ቢሮ ወደ እሳቸዉ እየገፏቸው ያሉትን ኃላፊነቶች ችላ ያሉ እንዳይመስላቸዉ ብለዉ አጥብቀዉ አልጠየቋቸዉም እንጂ።

የካቲት ሰባት ቀን ቀትር አካባቢ ዶ/ር ብርሃኑ የሚያሽከረክሯት መኪና በቡታጅራ መንገድ ከቡኢ ከተማ





አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ተገለበጠች። የጅማሬዉ ፍጻሜ ሆነ። የሐኪሙ፣ የተመራማሪዉ፣ የመምህሩ፣ የባለ ሥልጣኑ፣ የዓለም አቀፍ ሰባኪው፣ የአገልጋይ መሪዉ፣ የጸሐፊዉና የባለ ራዕዩ . . . ዶ/ር ብርሃኑ ሩጫ በአካል እዚች ነጥብ ላይ ተገታ።

ለቤተ ክርስቲያን፣ ለሕዝበ ክርስቲያኑ እና ለአገራቸው መልካምነት ከእግዚአብሔር የተቀበሏቸው ራዕይና ህልም ግን ከቶም ሊገቱ አይችሉም።

ኤክሌሺያም ትነሣለች! ተነሥታለችም። ተረኞች ከፍ አድርገው ያውለበልቡት ዘንድ ፋናውን ተረክበውታል። እነሆ ኑሮዉን ብቻ ሳይሆን ሞቱንና አሟሟቱን ጭምር የሚያዉቀዉን የዚያን የእግዚአብሔር ሰዉ ፈለግ እየተከታተልን ለመጻፍ አንድ አልን።


> **ዕድሜዬን እንደ ባረከዉ**
> **በምሬት - መሸተ በነጋ፣**
> **ሕይወቴን በዕዉቀት እንደ ኖርኩ**
> **በዕዉቀት ሰብስበኝ - አንተ - ጋ'።**

ለማለት የሚያበቃ ድፍረት የተጎናጸፈዉን የዚያን የእግዚአብሔር ሰዉ ፈለጎች በፊደል ጡቦች ገጣጥሞ ለማሳየት የተደረገዉ የመጀመሪያዉ ሙከራ እነሆ!

# 2. ሰውዬዉ

## 2.1. ስጅሬ፡ ቀበቶ ምሣዉ - ቀበቶ ራቱ!

ጣልያን በ1928 ዓም ኢትዮጵያን ወረረች። በአምስት ዓመቱ የአርበኝነት ዘመን ኢትዮጵያዊው ሕይወትና የአኗኗር ዘይቤ ተናጋ። በተለይም አርበኞች ጥቃት በሚያደርሱበት አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ ከሽፍታ ወግነሃል እየተባለ የግፍ ፅዋ ተጎነጨ፤ ተፈናቀለም። የከተማው ጭፍጨፋ ሲያይል ወደ ገጠር፣ ገጠሩ ሲያስጋ ወደ ከተማ መሰደድ የሕዝቡ ዕጣ ፈንታ ሆነ።



በጦርነቱ ሁለቱ ታላላቅ ወንድሞቻቸውን የአጡት አቶ ሀብቴ ወልደ ማርያም ከገጠሪቱ ኢትዮጵያ ወደ አዲስ አበባ ተሰደዱ። ቀደም ሲል ተሰደው የነበሩትን አክስታቸውን አፈላልገው ‹ብቅሎ ቤት› አካባቢ መኖር ጀመሩ። ያን ጊዜ ገና ለጋ ወጣት ነበሩ።

አርበኞችና እንግሊዞች አዲስ አበባን ሲቆጣጠሩ ተረኛው ተሳዳጅ ጣልያን ሆነ። የወደቀውም ባንዲራ ተመልሶ ቆመ። በነፃነት ማግሥት እንግሊዞች የመድፈኛ ጦር ጥንስስን ሲያቋቁሙ አቶ ሀብቴ ለመጀመሪያው ዙር ሥልጠና



ተመለመሉ። ሥልጠናውን ሲጨርሱ በወር አምስት ጠገራ ብር (ማሪያ ትሬዛ) ተቀጠሩ። በወቅቱ ምንዛሬ ብር 15.00 (አስራ አምስት ብር) ያህል ይገመታል።

በተመሳሳይ ዘመንና አጋጣሚ የቅርብ ዘመዶቻቸው ያለቁባቸው ወይዘሮ ዘነበች ወልዴም ነፍሳቸውን ለማዳን ወደ አዲስ አበባ መጥተው ይኖሩ ነበር። በ1939 ዓም አካባቢ ሁለቱ ስደተኞች ትዳር መሠረቱ። ተደላድለውም መኖር ጀመሩ።

አቶ ታምሩ ሀብቴ እንደ ሚሉት የሁለቱ ባለትዳሮች ባህርይ የእሳትና ውኃ ያህል ይለያያል።

አሥር አለቃ ሀብቴ በባህርያቸው ረጋ ያሉ፣ ቀጥተኛ፣ ውሸት የማይወዱ፣ ለእውነት ግምባራቸውን የማያጥፉ፣ ኩሩ መድፈኛ (በኋላም ኩሩ ፓሊስ)፣ ቀልድ፣ የዋዛና ፈዛዛ ወግ የማይሆንላቸው፣ ሲበዛ ታታሪና ትጉህ ሠራተኛ ናቸው። አለቆቻቸው ለሥራ ከመደቡባቸው ሥፍራ ለደቂቃ ንቅንቅ የማይሉ ቆፍጣና ወታደር ናቸው።

ከውትድርና ሙያቸው ሌላ ሁለገብ የቴክኒክ ችሎታም አላቸው። መኖሪያ ቤታቸው የተሠራው በአብዛኛው በራሳቸው እጅ ነው። አናጢነት፣ ግምበኛነት፣ ጭቃ ረጋጭነትና ለሳኝነት. . . የማይሞክሩት ሙያ የለም። ለዚህም እንዲረዳቸው የራሳቸው የድንጋይ መፍለጫ ዲጂኖ፣ መራጃ፣ መሮ፣ ሽብልቅ፣ ሙሉ የአናጢ ዕቃ (መጋዝ፣ ፋስ፣ መርቴሎ፣ መጥረቢያ፣ በለንኪኖ) አካፋ፣ ባሬላ፣ አላቸው። ገበሬም ናቸው። ሰፊ ጓሮቻቸውን መቆፈር፣ አዝርዕት





አትክልት ማልማት ከዓመት እስከ ዓመት የሚዝናኑበት ሥራ ነው።



የአጅሬ ልጆች፡ ታምሩ፣ ወንድሙ፣ ወለተችና ብርሃን

በአንፃሩ ባለቤታቸው ወይዘሮ ዘነበች የዋኅ፣ ገራገርና አዛኝ ናቸው። ‹‹የሳንቲሞችን የመጠንና የዋጋ ልዩነት ለይታ የማታውቅ ንጹህ፣ በሷ ከሚቆጣት መሬት ቢውጣት የምትመርጥ የዋህ ሴት ነች›› ይላሉ አራተኛ ልጃቸው አቶ ታምሩ። አሥር አለቃ ሀብቴ ይህ ባህርያቸው፣ ሥራ ወዳድነታቸውና ጠንቃቃነታቸው በሠፈራቸውም ሆነ በአደባባይ (በሥራ ቦታ) አስከብሯቸው ኖሯል። ‹‹አጅሬ›› የሚል ቅጽል ስም የተሰጣቸውም ለዚሁ ነው። እሳቸዉ ግን ራሳቸዉን ***‹‹እኔ የመድኃኒ ዓለም አሽከር! ቀበቶ ምሣዉ! ቀበቶ ራቱ!››*** ብለዉ ነዉ የሚጠሩት።

አጅሬ በሠፈርም ሆነ በመሥሪያ ቤት፣ ከአለቆቻቸውም ሆነ ከበታቾቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ሁልጊዜ ከመስመር



የአጆሬ ልጆች፦ ታምሩ፣ ወንድሙ፣ በቀለችና ብርሃን

ያልወጣ እንደ ነበርም ይነገራል፡፡ ስለሆነም ለቁም ነገር ጨዋታና ለምክር የሚፈልጓቸው ሰዎች በርካታ ነበሩ፡፡ አጅሬ ልጆቻቸው ልክ እንደ እሳቸው እንዲሆኑላቸው ብዙ ጥረት አድርገዋል፡፡ ልጆቻቸው እንደ ሃይማኖት አፅንተው እንዲይዙላቸው ደጋግመው የሚነግሯቸው አጭር መመሪያ ነበራቸው፡፡

*‹‹ተማር፣ አጥና! ሲሰለችህ ጓሮ ቆፍር፣ ሲርብህ ብላ፣ ሲደክምህ ተኛ!››* በቃ፡፡

መመሪያቸው በልጆቻቸው ሕይወት (በአብዛኛዎቹ) እውን ሆኗል፡፡ ስለሆነም ‹‹የሰፈር ሰዎች ልጅን ማስተማር እንደ አጅሬ፣ መማርም እንደ አጅሬ ልጆች›› ሲሉ ይደመጡ ነበር፡፡ የአጅሬ ልጅ ከእኒህ ኃይለኛ/ ብርቱ፣ ጥንቁቅ፣ ትጉህ፣ ሁለገብ፣ የሥነ ምግባር ሰው ሰብዕና ምን ያህሉን ወርሶ ይሆን?

## 2.2. ‹‹የቀበቶ ምሣው-ቀበቶ ራቱ ልጅ››

አጅሬ በመድፈኛ ወታደርነት ሲያገለግሉ በነበረበት ወቅት ይህ ነው የማይሉት ሕመም ታመሙ፡፡ ሆስፒታልም ገብተው በወራት ለሚቆር ጊዜ ተኙ፡፡ ገራገሯ ባለቤታቸው በወቅቱ ሦስተኛ ልጃቸውን ነፍሰ ጡር ነበሩ፡፡ ቀደም ብለው የወለዷቸው የአራት ዓመቷ ሴት ልጃቸውንና የሁለት ዓመቱን ወንድ ልጃቸውን በብቸኝነት ማሳደጉ ሳይበቃቸው ሦስተኛውን ለመገላገል ወራቸው ገባ፡፡ የኑሮው መድቀቅና ብቸኝነቱ ከበዳቸው፡፡ ሆኖም የተፈጥሮን ሂደት ማቆም አይቻላቸውምና ኑሮው የቀን ጨለማ እንደ ሆነባቸው ጥር 8 ቀን 1944 ዓም ሦስተኛ ልጃቸውን ተገላገሉ፡፡





አጅሬም ‹ድነሃል ቤትህ ግባ› ተብለው ከሆስፒታል ወጥተው በጋሪ ተሳፍረው ወደ ሠፈራቸው እየተጓዙ ነበር፡፡ በቅሎ ቤት ተብሎ ከሚታወቀዉ ሠፈር ዝቅ ብሎ፣ ከላንቻ ፊት ለፊት፣ ከኮንኮርድ ሆቴል አጠገብ ሚገኘው በዛን ጊዜ ስያሜው አቶ እሸቴ ድልድይ (አቶ እሸቴ የዛ አካባቢ ባለርስት ነበሩ) ከሚባለው ትልቁ ድልድይ አካባቢ ከነበረች የሣር ቤታቸው ሲደርሱ አዲስ እንግዳ ጠበቃቸው፤ እንደ ወንድ አያታቸዉ ብጭጭ ያለ ቀይ ወንድ ልጅ፡፡ ‹‹የቤተሰቡን ሕይወት የሚያበራ የተስፋ ብርሃን ሲሉ እንግዳውን ብርሃኑ›› ሲሉ ሰየሙት፡፡ ቀዮ ቅፅል ስሙ ሆነ፡፡


ብርሃኑ በልጅነት ዕድሜው

በእዉነትም ብርሃኑ - በጨለማ እንዳይዋጥ ፅኑ ምኞት የነበራቸው አጅሬ - ልጃቸውን በጥንቃቄ ለማስተማር ቆርጠዋል፡፡ እሳቤውን ከየት እንዳመጡት አይታወቅም፡፡

*‹‹ልጅ በተወለደ በ4 ዓመቱ ከ4 ወሩ ከ4 ቀኑ ትምህርት ሲጀምር እሳት የበላ ተማሪ ይሆናል››* የሚል እምነት ነበራቸው፡፡

ነገር ግን በጨቅላ ዕድሜው፣ ለዚያውም በሴሚስተሩ አጋማሽ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደ ማይቀበለው ተረዱ፡፡

ቢሆንም አማራጭ አላጡም። የቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን ካኅን የነበሩ አንድ መምህር ፊደል እንዲያስተምሩላቸው ብርሃኑን ልክ በ4 — 4 — 4 ዕድሜዉ በአደራ ሰጡአቸው። መምህሩ አንድ ልጅ ፊደል ለማስቆጠር በወር የሚያስከፍሉት አንድ ብር ብቻ ነበር። አጅሬ ግን ሌሎች ወላጆች የማያደርጉትን ለማትጊያ ብለው በወር አንድ የልብስ ሳሙና ጨምረዉ ይሰጧቸዉ ነበር። ጭማሪ ወጭ ለማውጣት የወሰኑት አቅማቸው ስለሚፈቅድ አልነበረም። ብርሃኑ ልዩ አትኩሮት ይሰጠው ዘንድ መምሕሩን ለማበረታታት እንጂ።

ብርሃኑ ቀለም ዘለቀው። ፊደል ቆጠራ፣ አቡጊዳ፣ ወንጌል፣ ዳዊት አጠናቀቀ። እስከ መጨረሻ ያልተላቀቃትን የፊደል አጣጣል ‹የቁም ጽሕፈት› ሲጀምር የፈጀበት ጊዜ አንድ ዓመት ተኩል ያህል ብቻ ነበር። በመስከረም ወር 1951 ዓም በመስቀል በዓል ማግሥት ‹የመድኃኒ ዓለም አሸከር፣ ቀበቶ ምሣው - ቀበቶ ራቱ› አጅሬ ሀብቴ ልጃቸዉን አስኳላ ትምህርት ቤት አስገቡት።የትምህርት ቤቱ ስም መርዕድ አዝማች ስብስቴ ነጋሢ ይባላል። በቀለች ሀብቴና ወንድሙ (አባቱ ሲጠሩት ወንድም አገኘሁ ማለቱ ይቀናቸዋል) ሀብቴም ትምህርት የጀመሩት እዚያው ነው።

አሁን ከመድፈኛ ወታደርነት ወደ ፖሊስ ሠራዊት የተዛወሩት የአሥር አለቃ ሀብቴ ደመወዝ ታምሩን ጨምሮ አራት ልጆች እያስተማረ ነው። ኑሮ ከበዳቸው። ቢሆንም መስዋዕትነት መክፈል ነበረባቸው፤ ያዉም - በደስታ። ድሮም ቢሆን ቁጥብ ነበሩ። አሁን ደግሞ በቀበቶአቸው አንጀታቸውን ደግፈው





ልጆቻቸውን በፅናት አስተማሩ። ሁሉም ጎበዞች ሆኑላቸው፤ የብርሃኑ ጉብዝና ግን ለየት ያለ ደስታን አጎናጸፋቸው።




ብርሃኑ ጀኔራል ዊንጌት ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪ ሳለ

የ4 - 4 -4 - እምነታቸዉ ሠራ። ብርሃኑ *በአስኳላ* ትምህርት ቤትም ኮከብ ተማሪ ሆነ። በዓመት ሁለት ክፍሎችን እየዘለለ ቀደም ብሎ ትምህርት ቤት የገባውን የልጅነት ጓደኛዉን ሚናስንና ታላቅ ወንድሙን ደረሰባቸዉ።

ከታላቁ ጋር አንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጠው መወዳደር ጀመሩ። ጭራሽኑ የታላቅ ወንድሙን የክፍል ማዕረግ ነጠቀ። ብርሃኑ አንደኛነቱን ሲያጠብቅ ያኛዉ ተከታይ ሆነ። በአምስት ዓመት የትምህርት ዘመን ስምንተኛ ክፍልን አጠናቀቀ።

የጄነራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ነፃ የትምህርት ዕድል ለማግኘት ፈተና የተቀመጠውም ከወንድሙ



ብርሃኑ ጀኔራል ዊንጌት ት/ቤት የ9ኛ
ክፍል ተማሪ ሳለ

ሀብቴና ከቅርብ ጓደኛው ሚናስ ብሩክ ጋር ነበር። አሁንም ሁለቱንም ጥሎ አለፈ። ቀበቶ ምሣው በቀዮ ኩራት ተሰማቸው። ለመጀመሪያ ጊዜ ከጉያቸው ርቆ ዊንጌት አዳሪ ትምህርት ቤት የሚገባውን ልጃቸውን ለመሸኘት መዘጋጀት ጀመሩ።

‹‹ወጪው የፈጀውን ይፍጅ እንጂ አሁን ከተለያዩ ውድቅዳቂ ነገሮች ሠርቶ የሚጫማውን ጫማ አድርጎ አይሄድም›› አሉ። ምን የመሰለ ሸራ ጫማ በሁለት ብር ከሃምሳ ሣንቲም ገዙለት። ካልሲ ችግር የለም፤ ለዩኒፎርም ከሚሰጣቸው የወታደር ካልሲ ሁለቱን አካፈሉት።ልብሶቹን ሚሸክፍበት ሻንጣ በአራት ብር ገዙለት። የዓመቱ ትምህርት የሚጀመርበት ዕለት አባትና ልጅ በአውቶቡስ ተሳፍረው ወደ ጊዮርጊስ አብስ አሉ።

የቀዮን ነገር በዊንጌት ትምህርት ቤትና በእግዚአብሔር እጅ አኑረው ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ከሳምንታት ቆይታ በኋላ ቤተሰቡን ለመጠየቅ ሲመጣ *‹ሁለመናው ተለውጦ ነበር›* ይላሉ አቶ ታምሩ፡-

> *‹‹ቁምጣና ሸራ ጫማ አድርጎ የሄደው ብርሃኑ ሰማያዊ ቀለም*
>
> *አንገትያ (V) ሹራብ፣ ካኪ ቦላሌ፣ አስኮ ቆዳ ጫማ፣ አድርጎ መጣ። ‹ልጁ ቀዮ የመኳንንት ልጅ መሰለ እኮ!› አለ አባታችን።››*

ቀዮ ለቤተሰቡ አባላት ብቻ ሳይሆን ለሠፈሩ ልጆችም ይብሱኑ ብርቅ ሆነ። በቅዳሜና  እሁድ ቆይታው አዲሱ የሕይወት ጅማሮው ምን ዓይነት እንደሆነ ሲጠይቁትና ሲያወራቸው ሰነበተ።





‹‹ፍርኖ ዳቦ እንደ ልብ ስለመገኘቱ፣ እሱ የሚኖበት የተማሪች ሕንፃ ‹ግሪን ሃውስ› እንደሚባል፣አንድ አልጋ ላይ ለብቻው እንደሚተኛ፣ የአንሶላውን ልስላሴ፣ የብርድ ልብሱን መኮስኮስ በሥዕላዊ ትረካ ሲነግራቸው፤ በየወሩ የሚሰጠው የኪስ ገንዘብ አሥረኛ ክፍል ሲገባ እንደ ሚጨመርለት. . .ወዘተ።››

ተጨማሪ አዳዲስ ነገሮችን ለመስማት ሲሉም ወደ ቤተሰብ የሚመጣባቸዉ ቀናት በጉጉት የሚጠበቅ ብርቅ ልጅ ሆነ። የዊንጌት ቆይታው በጨመረ መጠን ለቤተሰቡና ለሠፈር አቻዎቹ የሚተርካቸው ቁምነገሮች ፍፁም እየተለወጡ ሄዱ።



*ወንድምአገኘሁ እና ብርሃኑ ሀብቴ*

በተለይም በትምህርታዊ ጉዞዎች ስለ ጎበኛቸው ቦታዎች የሚነግራቸው ነገሮች ሁሉ አስደናቂ ሆኑባቸው።



ወንድምአገኘሁ እና ብርሃኑ ሀብቴ

‹‹የላንጋኖ ሐይቅና የአካባቢው ውበት፣ የአምቦ የመዋኛ ሥፍራ፣ ስለ እንጦጦ ተራራና ጫካ፣ ስለ ዱር አራዊቱ. . .ወዘተ የአተራረክ ችሎታው ያስደምማቸዋል፡፡

የአራት ዓመት ታናሽ ወንድሙ ታምሩ በቀዮ ትረካ ከተማረኩት አንዱ ነበር፡፡ ስለሆነም፡- ‹‹ብርሃኑ ቤት እያለ ራስጌና ግርጌ ሆነን ለአራት የምንተኛበት አልጋ እሱ ከሄደ በኋላ ‹የተሻለ ቢጠበንም› ለእረፍት በመጣ ቁጥር የሚነግረኝ አዳዲስ ነገሮች ለመስማት ስል ቶሎ ቶሎ ቢመላለስ› ይወድ እንደነበር ይናገራል፡፡

ታላቅ ወንድሙ ወንድም አገኘሁ ሀብቴ የሚመኘው ከዚህ የተለዩ ነበር፡፡ ያም ቀደም ሲል በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንደኝነት ለመውጣት የሚያደርጉትን ፉክክር ዩኒቨርሲቲ ተገናኝተው እንደገና መቀጠል፡፡ ግን እግዚአብሔር ያልፈቀደውና ምኞት ብቻ ሆኖ ቀረ፡፡ ወንድሙ (ወንድም አገኘሁ) ሀብቴ የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ሳለ በተወለደ በ17 ዓመቱ ሰኔ 17 ቀን 1959 ዓም አረፈ፡፡ የወንድሙ ሀብቴ ሞት ለቤተሰብ ታላቅ የልብ ሥብራት ሆነ፡፡ *‹ቀበቶ ምሣው - ቀበቶ ራቱ ሆኜ የአሳደግሁት ልጄን ተነጠቅኹ››* አሉ አሥር አለቃ ሀብቴ፡፡

ወንድሙ የሞተው የአሥራ አንደኛ ክፍል የመጨረሻ ሴምስቴር ፈተና በመውሰድ ላይ ሳለ እንደ ነበር ያስታውሷል፡፡ ይህ ማለት ብርሃኑም የወንድሙን መርዶ የሰማው ፈተና ላይ ሆኖ ነበር ማለት ነው፡፡ ከፈተና በኋላ ለክረምት ዕረፍት ትምህርት ቤት ተዘጋ፡፡ ብርሃኑም የእረፍት ጊዜውን ለማሳለፍ ወደ ቤተሰቡ መጣ፡፡ ለአራት ከሚተኙበት





አልጋ ወንድሙን ሲያጣው በፍርሃት ተዋጠ፡፡ መሸሸጊያ እስከ ሚያጣ ድረስ የፍርሃት ጣዕረ - መንፈስ አሳደደው፡፡ በዚህ ወቅት ነበር፡- ስለ ሞትና ሕይወት፣ ስለ ፅድቅና ኩነኔ፣ ስለ ገነትና ሲዖል፣ የእነዚህ ሁሉ ምስጢራት መዝገብ እንዲሁም የጥያቄዎች ሁሉ መልስ ስለ ሆነው ‹‹እግዚአበሔር›› መመራመር የጀመረው፡፡

በዚህ የብቸኝነት፣ የራቁትነት፣ የአለኝታ ቢስነት ስሜት ውስጥ እያለም ነበር የዘላለም አምባ የሆነውን ጌታ እግዚአብሔርን የተቀበለው፡፡ ዝርዝሩን ‹ክርስቲያን ብርሃኑ› በሚለው ርዕስ ይመልከቱ፡፡

## 2.3. *የልጅ ልባም*

የብርሃኑ ጄነራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መግባት የቤተሰቡ ሕይወት መለወጥ ብሥራት ሆነ፡፡ የአመት ልብስ፣ ጫማ፣ የትምህርት ቁሳቁስና የተደራጀ የጋራ መኝታ ቤት የሚሰጠው ትምህርት ቤቱ ነው፡፡ በዚያ ላይ የኪስ ገንዘብ በወር ሁለት ብር ከሀምሳ ሳንቲም ይከፈለዋል፡፡ ሽራፊ ሳንቲም ያለአግባብ አያጠፋም፡፡

ብርሃኑ በጂኦግራፊ ትምህርት ጎበዝ ነበር፡፡ የላቀ ችሎታውን የተገነዘቡት መምህሩ ጄሲ ሮይድስ ወደ አሥረኛ ክፍል እንደተዛወረ የጂኦግራፊ ክበብ አባል እንዲሆን ገፋፉት፡፡ ቀጥሎም በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ በነበረው የሜትሮሎጂ ጣቢያ የትርፍ ሰዓት ሠራተኛ አደረጉት፡፡ የወር ደመወዙም አርባ አምስት ብር ነበር፡፡ የኪስ ገንዘብ ሲጨመርበት የወር ገቢው ከአባቱ ደመወዝ በለጠ፡፡ ኢንግዲህ አባትና እናቱን

መርዳት የጀመረው ገና በአሥራ አራተኛ ዓመቱ ነበር ማለት ነው። አጅሬ ‹‹ቀበቶ ምሣ - ቀበቶ ራቱ›› ኑሮአቸው መለወጥ የጀመረውም ከዚያን ጊዜ አንስቶ ነው። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት የስኮላር ሺፕ አሸናፊ ሆኖ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ ደግሞ በየወሩ አንድ መቶ ብር የኪስ ገንዘብ ይቆረጥለት ጀመር። ይህንንም ቢሆን ወደ ራሱ ኪስ አልከተተውም።

ለነገሩ የአጅሬ ልጅ የቤተሰቡን የኑሮ ሸክም መጋራት የጀመረው ገና በህፃንነት ዕድሜ ነው፤ ቢያንስ ራሱ ሸክም ሆኖ አያውቅም ይላሉ አቶ ታምሩ ሀብቴ።

> *ብርሃኑ ገንዘብ አጥቶ አያውቅም። እኔ ከመሬት ካላገኘሁ በስተቀር ሳንቲም በእጀ ነክቼ አላውቅም። አባታችን ሱቅም አይልከንም። ዐረብ ቤት (ሱቅ) ልጆችን መላክ መልቲ ያደርጋል ይላል። ያኔ የ05 ሣንቲም ስኳር ገዝቶ ጠጠር ከረሜላ (ሽፋን የሌለው) የሚመረቅበት ዘመን ነውና ጣፋጭ ነገር ልጆችን ያበላሻል በሚል ይመስለኛል። ለነገሩ ጠቅሞናል።*
>
> *ብርሃኑ ለሠፈሩ ሰዎች ጋቢ፣ ነጠላ ይቋጫል። ተመኑን ባላስታውሰውም ክፍያ ይቀበላል። ለዘመን መለወጫ ነጭ ወረቀት ገዝቶ የተለያዩ ቅጠላ ቅጠሎች ጨፍጭፎ ቀለም ጨምቆና አዘጋጅቶ «እንኳን ከዘመን —— ወደ ዘመን —— አሸጋገርዎ» የሚል ጽሁፍ በመፃፍ አበባ አዘጋጅቶ ለሠፈር ልጆች እንደ ጅምላ ሻጭ ሆኖ ያከፋፍላል። በዚህም ገንዘብ ያገኛል።*
>
> *ከሠፈር ልጆች ላቅ ያለ የፈጠራ ችሎታ ስላለው የሽቦ መኪና በመሥራት ትክክለኛ የመኪና /የአውቶሞቢልም ሆነ ገልባጭ ቅርፅ/ በመስጠት የተለያዩ ቀለሞች ያላቸው ካርቶኖች ወይም ወረቀት በመሸፈን በጥሩ ዋጋ ይሸጣል። የወረቀት ኖት ብዙ*





> *ባላይም ነጫጭ ሳንቲሞች (ሽልንጎች) ይቀበላል። እነዚህን ሁሉ ያጠራቅማል፤ ያስቀምጣል።*
>
> *ብርሃኑና ወንድሙ በጥናት ላይ በጣም ያተኩራሉ እኔም በዚህ ተከትያቸዋለሁ። አምሽተው አያጠኑም፤ ኩራዛችን በጊዜ ስለሚጠፋ በከንቱ አታቃጥሉም ስለሚባል። ታዲያ ብርሃኑ ወፍ ሲንጫጫ ከቤት ቀስ ብሎ ወጥቶ በወጋገን እስከ ሚነጋ ድረስ ያጠናል።*
>
> *ብርሃኑ ትጉና ንቁ ነው። 8ኛን ጨርሶ 9ኛን ክፍልን ለመጀመር ወደ ጀነራል ዊንጌት ት/ቤት እስከ ተሻገረ ድረስ ጫማ ስለ ሌለው በባዶ እግሩ ነበር የሚሄደው። ሆኖም ከየት እንደ ሚያገኛቸው በወቅቱ ባለውቅም ለወራት የሚያዘልቁት የተደራረበ የካርቶን ሶል ያላቸውና በላስቲክ የተሸፈኑ ዘለበት ጭምር ያላቸው ነጣላ ጫማዎች እየሠራ ይጫማ ነበር እንጂ የአባቱን እጅ አይጠብቅም ነበር።*

## 2.4. ቤተ መንግሥት

*የመድኃኒ ዓለም አሽከር፣ ቀበቶ ምሣው - ቀበቶ ራቱ - አጅሬ የአሥር አለቃ ሀብቴ በህልማቸው በእውናቸው ያላሰቡት ወግ ደረሳቸው፡፡* አዎ በመስከረም ወር 1960 ዓ.ም ቤተ መንግሥት ተጋበዙ፡፡



*ብርሃኑ ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እጅ ሽልማት ሲቀበል*

በዚያን ዘመን በጦር ሜዳ የተለየ ጀብድ የሠሩ፣ አገርን የሚያስጠራ ታሪክ ቀያሽ (እንደ እነ አበበ ቢቂላ) ድርጊት በአደባባይ የሠሩ ካልሆነ በስተቀር የልዑላን ቤተሰቦች፣ ባለሥልጣኖች፣ የመኳንንት ዘሮች እንጂ ተራው ኢትዮጵያዊ በንጉሡ ቤተ መንግሥት የሚጋዝበት ዕድል እጅግ ጠባብ ነበር፡፡





በብላቴንነቱ ታሪክ መሥራት የጀመረው ልጃቸው አማካኝነት ግን ይህን ማዕረግ ተጎናጸፉ፡፡ በሃዘን የተመታው ልባቸውም በተስፋ ለመለመ፡፡ የአራት ዓመት ታላቅ ወንድሙ በሆነው በብርሃኑ አርዓያነት ሕይወቱን እየሞረደ የነበረው ታምሩ ትዕይንቱን በልጅነት አእምሮውና በጉልማሣነት ብዕሩ በደንብ ቀርጾታል፡፡ እነሆ፡-

*በክረምቱ የነፍሱን ጌታ ተቀብሎ መስከረም ሲጠባ የ12ኛ ክፍል ትምህርቱን የጀመረው ብርሃኑ የ2ኛ ደረጃ የትምህርት ሕይወቱን በማገባደድ ላይ ይገኛል፡፡ ለ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ዝግጅት ላይ ነበር፡፡ ከ11ኛ ክፍል ጀምሮ ሰውነቱ ተለውጧል፡፡ ቁመቱ አድጓል፡፡ ወንድሜ ስለሆነ ካላበዛሁት በስተቀር ውብና ብሩህ ተስፋ ፊቱ ላይ የሚነበብበት የተረጋጋ በራሱ የሚተማመን በሰፈሩ ወጣቶችና ነዋሪዎች ዘንድ ተወዳጅነትን፣ ፍቅርንና ከበሬታን የተጎናፀፈ እንደ ነበረ መናገር ይቻላል፡፡ ለሁሉም በሁሉም የሚታመን ወጣት ነበር፡፡*

*ትጉሁ ተማሪ ብርሃኑ ከፈረንሳይኛ ቋንቋ፣ ግዕዝና የታሪክ ትምህርት በስተቀር ቀሪዎቹን ዘጠኝ ትምህርቶች ለፈተና ተመዝግቧል፡፡ እኔም እንደ አቅሜ የስድስተኛ ክፍልን ሚኒስትሪ ፈተና ለመውሰድ እየተዘጋጀሁ ነበር፡፡*

*አባታችን ልጁ ኮሌጅ በጥሶ «ዩኒቨርስቲ» ከሚገባ አባዲና ፖሊስ ኮሌጅ ገብቶ ኮከብ ቢጭንለትና ለዘመናት መድፈኛ ሆኖ ከዛም ቀጥሎ የፖሊስ ሠራዊትን ከተቀላቀለ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን በተራ ወታደርነት ያገለገለበት ቁጭቱን ቢወጣለት ነበር ምኞቱ፡፡ በሀሳቡ እንዲስማማለት በቁልምጫና በስስት ጠይቆታል፡፡ <u>ሆኖም ከልጅነቱ ጀምሮ ከአባቱ የወረሰው በራስ ምርጫና ዉሳኔ የመመራት ዝንባሌ አሁን ደግሞ በራሱ ማንነት የበለጠ በመታደሉ ነው መሰለኝ መሐንዲስ የመሆን ምኞቱ ያየለበት ወቅት ነበር፡፡</u>*

*በዛን ዘመን የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ሁሌም በትንሳኤ ማግሥት ስለነበረ ብርሃኑ በኋሉን ከኛ ጋር ውሎ ከሰዓት*



ብርሃኑ ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እጅ ሽልማት ሲቀበል

ረፊድ ካለ በኋላ ወደ ዊንጌት ለመሄድ ተዘጋጀ:: ሁሌም ዕቃም ሲወድቅበትም - ሲደናቀፍም የመድሃኒ ዓለም ባሪያ እያለ የሚፎክረው አባታችን የኔ መድሃኒዓለም የምጠጣው ጽዋ አለልህ ብሎ ሸኘዉ:: እጅግ ከፍተኛ ውጤት አምጥቶ አለፈ:: የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ሽልማት ድርጅት የነፃ ትምህርት ሽልማት ሰጠዉ::

ከንጉሡ እጅ ሽልማቱን ለመቀበል በታላቁ ቤተመንግሥት ከመሰሎቹ ጋር ቀጠሮ ተይዞለታል:: በወትሮ ሥራው አማካኝነት የምኒሊክን ቤተመንግሥት ለመጠበቅ በስተቀር እልፍኝ አዳራሹን አይቶ የማያውቀዉ አባታችንም ተጋብዞ ነበር:: መጪው ዓመት ሽራ ጫማ በተሰፋ ለማጥለቅ ለእግር ማለስለሻና ማለማመጃ የቼኮስሎቫኪያ የ6 ብር ቦቲ ጫማ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጫማው እግረኛውና ቁምጣ ለባሹ ታምሩም እንኳን ዛሬ በደስታና በኩራት ያስታዉሰዋል:: ወትሮም እየተወረወረ ከሚራመደው አባቱ ጀርባ ኩስ ኩስ እያለ ቤተመንግሥት የተባለውን ጉድ ለማየትና የወንድሙንም በዓል ነገ ለጓደኞቹ በኩራት ለማውራት ተሰፋ ሰንቆ ከቤተመንግሥቱ በር ደረሰ::

ወደ ግቢ ስንደርስ ቡሽ ባርኔጣ የደፋ ጎፈርና አንጎፈር ያደረጉ የክብር ዘበኞች ወዲያ ወዲህ ይንጎራደዳሉ:: ከአባቴ ጋር ተነጋገሩ፣ «ዛሬ ልጁ ንጉሡ ፊት ይቀርባል፣ ይሄም ትንሹ ልጁ ነው» አላቸዉ:: እንኳን ደስ አለህ ግባ አሉት:: ያው ፊትና ኋላ መሆናችን እንደ ተጠበቀ ሆኖ ዘለቅን:: የአባታችን ዓይን ግራና ቀኝ ሲያማትር ያው እዛ ሜዳላይ ብርሃኑ ተሰልፏል አልኩት::

ብርሃኑ ከፊት ለፊት ከተሰለፉት መሃከል ነበር:: ቁመቱ ዘለግ ያለ ቢሆንም የተሰለፈው ከአጫጭሮቹ ፊት ነው:: ዛሬ ሰልፍ በቁመት አይደለም:: እኛ በፍጥነት ወደ አዳራሹ ገባን:: ጥግ ላይ ወታደራዊ ልብስ የለበሱ ሙዚቀኞች ቆመዋል:: በሌላኛው ጥግ ደግሞ የአገር ልብስ የለበሱ ሴትና ወንድ ሙዚቀኞች ይታያሉ::





ጠረጴዛና ወንበሮች የዙፋንና የዘውድ ምልክት ታትሞባቸው ጥግ ጥግ ይዘዋል:: በቀይ ከፋይ ያጌጠ ዙፋን ተቀምጧል:: እግሮቹ የአንበሳ እግር ቅርፅ ኖሯቸው ወርቅ ቅብ የተቀቡ ናቸው:: በዙፍኑ አቅጣጫ ከፍት ሲሆን ዙሪያውን እኛና የኛ መሰል ታዳሚዎች ተኮልኩለዉበታል:: ሰው ግን እየበዛ በመሄዱ እኔን ከመቀመጫ እንዳስነሱኝ አባቴም አላወቀም ነበር:: ተንጠራርቼ ሳየው አይኑ ፈጦ ቀጥ ብሎ ቆሟል:: ግፊያው አስመርርሮኛል:: በመጨረሻም ወደ ኋላ ወጣሁ::

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ንጉሡ ገቡ:: እልልታውና ማርሽ ሙዚቃው ቀለጠ:: ልቤ በውስጤ ተንቀጠቀጠች:: ብዙም አልቆየ ፀጥታ ሆነና ስም ይጠራ ጀመረ:: ብርሃኑ ሀብቴ ከጀኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት እጅግ በጣም ከፍ ባለ ማዕረግ ሲል ሳላውቀው ወንድሜን ለማየት ብዬ ራሴን ሉልና ዘውድ የታተመበት ጠረጴዛ ላይ ከነቦት ጫማዬ አገኘሁት:: ወንድሜ የተጠቀለለ ነገር በትምህርት ሚ/ሩ አቅራቢነት ከጃንሆይ እጅ ተቀብሎ በፈገግታ ወደ መጣበት ሲመለስ ለካ አጠገቤ ክቡር ዘበኛ ደርሶ ኖሮ ዘልዬ ብወርድና ብሽሎከለክም በመጨረሻ ይዞኝ ሁለቱን ጆሮዬን አንድዶና አንጥቶ ከግቢ አስወጣኝ:: እያለቀስሁ በፊት በር በኩል አድርጌ ቁልቁል ወደ በቅሎ ቤት በእግሬ ወረድሁ::

የሆነው ቢሆንም እኔና አባቴ በብርሃኑ የተነሳ ለቤተመንግሥት በቅተናል:: አባቴም ለጎረቤትና ለእንግዶች ለጓደኞቹ እየገለፀ እድሜ ለልጄ እያለ ሁሌም ያነሳው ነበር እኔ ደግሞ እስከ ዛሬ አስታውሰዋለሁ:: ብርሃኑንም ቤተሰቡን ለቤተመንግሥት ያበቃ ብዬዋለሁ::

## 2.5. <ሕንቨርሲቲ>

ዕድሜ ልካቸውን በመድፈኛ ወታደርነትና በፖሊስነት አገልግለው የደረሱበት ከፍተኛ ማዕረግ የአሥር አለቅነት ነበር። የወር ገቢያቸውም ከአርባ አምስት ብር አልዘለለም። የአባት ያህል የሚበልጧቸው ወጣቶች በሆለታ ገነት የጦር

ት/ቤትና፣ በአባዲና ፖሊስ ኮሌጅ ገብተው ተምረው፣ ከዚያም መኮንን ሆነው መጥተው አዛዣቸው ሲሆኑ አይተዋል። እሳቸው ግን ዳግም ካልተወለዱ በቀር ይህን ዕድል መልሰው አያገኙትም። ነገር ቁጭታቸውን የሚወጡበት አንድ ተስፋ በውስጧቸው ተተክሏል፤ ብርሃኑ።

ብርሃኑን አባዲና ፖሊስ ኮሌጅ እንዲገባላቸው አባብለውት ነበር። የእርሱ ፍላጎት ግን መኮንን ሳይሆን ኤንጂነር መሆን ነበር። በኋላ ግን ሀሳቡን ቀይሮ ሕክምና አጠና። ብርሃኑ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሳለ በአንድ አጋጣሚ ያስቀየማቸውን ወጣት መኮንን አጅሬ እንዲህ ብለውት ነበር፡- *‹‹የኔ ቀበቶ ምሣው - ቀበቶ ራቱ ልጅ ንቆት እንጂ ዩንቨርሲቲ የገባው ኮከቡን ይደረድረው ነበር።››* ዝርዝር ታሪኩ በታምሩ የትውስታ ማህደር ውስጥ እንደተተከለ እስከ አሁን ድረስ አለ። እንደሚከተለዉም ይተርኩታል፡-

. . . ብርሃኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምናልባትም የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሆኖ ይመስለኛል ስደት ይነሳና ተይዞ አንደኛ ፖሊስ ጣቢያ ይታሰራል። ይህም ለአባታችን ይነገረዋል። ጠረ - ማርያምና ሚሲዮን ሆነ ብሎ የተናደደ ቢሆንም አለኝታው ልጁ ነውና ወደሱጋ ለመሄድ ይዘጋጃል። እኔም አጠገቡ ነበርኩና በድንገት በል፣ ወንበር ላይ ወጥተህ ያንን ፎቶ ግራፍ አውርድና በጋዜጣ ጠቅልለው አለ። ፎቶግራፉ ብርሃኑ 12ኛ ክፍል ሲጨርስ በምኒሊክ ቤተ መንግሥት ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሽልማቱን ሲቀበል የተነሳውና በቤታችንም ከፍ ብሎ ከተሰቀለው ከመድሃኒዓለም ምስል በታች ተንጠልጥሎ የሚገኘው ነው።





አውርጄ ከጠቀለልኩት በኋላ እሱ በሃሣቡና በውስጡ ቁጭት እየተነዳ ቀርቶ ወትሮም እየተወረወረ ስለሚራመድ እኔ ከኋላው የሩጫ ያህል እየተከተልኩት በደብረዘይት መንገድ ላይ አሁን ግሎባል ሆቴል ያለበት አካባቢ ባለው አውቶቡስ ማቆሚያ እንደደረስን ድንገት በመጣቸው አውቶቡስ ላይ ተሳፈርን። በተለመደው ሁኔታ መሿለኪያ ከመድረሳችን በፊት ወደ ግራ ታጥፈን በጨርቆስ ቤተክርስቲያን በኩል ወደ ፖፖላሬ አቅጣጫ ቀጠልን። በመጨረሻ አዲስ አበባ ፖሊስ ዋና ጽ/ቤት ደረስን።

ከዚያም ወደ አዛዥ ቢሮ አመራ። አዛዡ ቢሮ በር ላይ ለሚጠብቀው ፖሊስ ጉዳዩን ነገረው መሰለኝ እንዲገባ ፈቀደለት። እኔም ያቺ በጋዜጣ የተጠቀለለችዋን ፎቶ ግራፍ ይዤ አባቴን ተከትዬ ዘው አልኩ። ሰውነትን በሚነዝር እንቅስቃሴ ዓይነት በወቅቱ አዣዥ ለነበሩት ለኮለኔል ወንድሙ ሰላምታ ሰጥቶ እንዳበቃ ይተዋወቃሉ መሰለኝ አጅሬ ለምን መጣህ አሉት? ያኔ ያቺን በጋዜጣ የተጠቀለለች ፎቶ ግራፍ ገልጦ እያሳያቸው፣ *«ጌታዬ ለአገር የሚጠቅም ልጇ ታስሯል። እኔ መሃይሙ ልታሰርና እሱ ይለቀቅልኝ ኮሌጅ በጥሶ የገባ፣ ቀበቶ ምሳ ቀበቶ ራቱ ሆኜ ያሳደኩት ልጄን ነው አንደኛ ፖሊስ ጣቢያ ከትምህርት ሲወጣ ወስደው አስረውታል»* በማለት ይገልፅላቸዋል።

እሳቸውም በእርጋታ ካዳመጡ በኋላ አይዞህ ብለው እንደቆሙ ከጎናቸው ያለውን ስልክ አንስተው ከአንደኛ ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ በአባቱ ዋስትና እንዲፈታ ይስማማሉ። ይህንኑ ያስረዱታል። አባታችንም አመስግኖና በተለመደው ሁኔታ ሰላምታ ሰጥቶ በአሸናፊነት፣ በደስታና በቁጭት ልጁን ሊያስፈታ ፖፖላሬ ከደረስንበት ሁኔታ ባልተናነሰ የፍጥነት ጉዞ ሽቅብ ወደ 1ኛ ፖሊስ ጣቢያ አመራን።

ወደ አዛገፑ ቢሮ ሲያቀና ለካስ ውጭ ነበረና ይገናኛሉ፡፡ አስቀድሞ መልዕክቱ ስለ ደረሰው ባለ ጉዳዩን አውቆታል፡፡ ወጣቱ አዛዥ አንድ ነጠላ ኮከብ ነው ያለችው፡፡ አባቴ ቀዝቀዝ ያለ ሰላምታ ሰጥቶ ከኮለኔል ወንድሙ ቢሮ መምጣቱን ይነግረዋል፡፡ «ወጣቱ መኮንንም ልጅህን ቀጥተህ አታሳድግም ሥራ ትተህ ወዲያና ወዲህ ከምትል አንተን አጋዴን መላክ ነበር» ይለዋል፡፡ በዛን ጊዜ የሆነው ሁኔታ እጅግ በጣም ያልተጠበቀ ከብዙዎች ጋር በሠራዊቱ ውስጥ ለብዙ ዓመታት በትጋት ሠርቶ በርካታ ከፍተኛ መኮንኖች ለሚያውቁትና በሥራው ለሚያመሰግኑት በቅርብ ጊዜ ደግሞ ፲ አለቃ ለሆነው አባታችን የዚህ ወጣት መኮንን ምላሽ ንቀት መስሎ ታየው፡፡ ወትሮውም ልጁ አባዲና ፖሊስ ኮሌጅ እንዲገባ ሲመኝ የነበረው ትዝ አለው፡፡ መሰለኝ፣ «የኔ ልጅ ንቆት ኮሌጅ ገባ እንጂ ኮከቡን ይደረድረው ነበር፡፡ ቀጥቼ በጨዋነት ያሳደኩት ልጄን ልትሰድበው አይገባም» በማለት በንዴት እየተቁነጠነጠ መለሰለት፡፡

በቆዳ ቀበቶው ላይ የታጠቀው ሽጉጥ ይወዛወዛል፡፡ ነገሩ አላማረኝም፡፡ ወታደር ፖሊሶች ሀብቴ ተው ይላሉ፤ ያውቁታል መሰለኝ፡፡ ነገሩን ለማብረድ ይጥራሉ፡፡ የዚህ ወጣት መኮንን ንቀት አዘል ንግግር ለነሱም የተዋጠ አልመሰለኝም፡፡ ነገሩን ሲያቀዘቅዙ እንጂ አባቴን ሲፈታተኑት አላየሁምና፡፡

በመጨረሻም ግርግሩ ሰክኖ ብርሃኑ ከታሰረበት ክፍል ተጠርቶ ፊት ለፊታችን ቆሟል፡፡ አባቱም ድል አድራጊ ሆኖ ልጁን በማውጣቱ በፊቱ ላይ ኩራት ይነበባል ከጥቂት ጊዜ በኋላም ይዞት ሊሄድ ነው፡፡ ወጣቱ መቶ አለቃም ለወደፊቱ ታረም ለዛሬው በአባትህ ዋስትና ትፈታለህ ይለዋል፡፡ አባቴም ሆነ መቶ አለቃውም ያልጠበቁት አንድ ነገር ሆነ፡፡ ብርሃኑ በእርጋታ "እኔ ምንም ያጠፋሁት ነገር ስለሌለ በራሴ እንጂ





በአባቴ ዋስትና አልወጣም" ይላል፡፡ ብርሃኑ ወደ ማረፊያ ቤቱ፣ መቶ አለቃውም ወደ ቢሮው፡፡ ፊቱ አጋም የመሰለው አባታችንም እኔን አስከትሎ ቁልቁል ወደ ስድስት ኪሎ፡፡

በንዴት የጦዘው አባታችን «ልጄ አዋረደኝ አይደል፤ ዛሬ እክደዋለሁ» እያለ ጉዟችንን ቀጥለን መሿ ለኪያን ዝቅ እንዳልን ለነፍስ አባቱ በአስቸኳይ እንዲመጡለት መልዕክት ልኮ ወደ ቤታችን በቅሎ ቤት አለፍን፡፡ እንደገባም ወረቀትና እስኪሪብቶ አዘጋጅቶ እየተጠባበቀ ሳለ ብዙም ሳይቆይ መምሬ ወልደተንሳይ ምን ክፉ ነገር ደረሰ ብለው ከተፍ አሉ፡፡ ነገሩን በንዴት አጫወታቸው፡፡ «ከአሁን በኋላ ልጄ አይደለም፡፡ ዛሬ እክደዋለሁ፡፡ ይህንኑ በርሶ ፊት ተፅፎ በኮቢ ይፈረምልኝ» አላቸዉ፡፡ እሳቸው ግን አረጋግተውት ልጅ ነው ይመለሳል ብለውት ሃሣቡን ያስተውትና ሌላ ጫወታ ጀመሩ፡፡ ብርሃኑም በማግስቱ ይሁን በሁለተኛው ቀን እንዳለው በራሱ ዋስትና ፈርሞ ከአንደኛ ፖሊስ ጣቢያ በነፃ ተለቀቀ፡፡ በራሱ ዋስትና፡፡

# 3. ክርስቲያን ብርሃኑ

ፍቅርህ ፈለቀቀኝ - ከዓለም አባራ፣
በደምህ ነፃሁኝ - በመስቀልህ ሥራ፤
ሳላውቅ መታወቄ - ሳልደዝህ መያዜ፣
አባትም እናትም - ሥራ ደመወዜ፣
ሁሉንም! ሁሴንም! . . . በብቸኝነቴ፣
የሆንከልኝ አምላክ . . .፣
እግርህ ስር ሳኑራት - ደቼዉና ሀብቴ፣
ለአሥራ - ለንት ዓመቴ ወራት የጎደላት፣
ገና - ድንግል -ገና - አፍላ ልጅነቴን፤
እነሆኝ ዉረሳት!
ጮርቃነቴን ወስደህ - ለራስህ አብስላት፡፡

*(ካልታተመ ጥራዝ)*

## *3.1.‹‹በልጅነታችን አገኘን››*

1954 ዓም በሰብስቴ ነጋሢ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ነበር፡፡ በ2ኛ ሴምስተር ወደ ስድስተኛ ክፍል ሲዛወር ደረሰብኝ፡፡ የሠፈር ልጆች ስለሆንን አንድ ክፍል ውስጥ መገናኘታችን የበለጠ አነቃቃን፡፡ በ1955 ዓም በአንደኛው ሴሚስተር ጥሩ ውጤት አመጣን፡፡ ሁለታችንም ወደ ስምንተኛ ክፍል ተዛወርን፤ ሁለቱን ክፍል በአንድ ዓመት ጨረስን፡፡ የሚኒስትሪን ፈተና አብረን ወሰድን፡፡

ዘጠነኛ ክፍል ማለፋችንን ስናውቅ የጄነራል ዊንጌት ትምህርት ቤት ስኮላርሺፕ እንዲሰጠን ለማመልከት አብረን ሄድን፡፡ አብረን የመግቢያ ፈተና ወሰድን፡፡ እሱን ተቀበሉት፡፡ እኔ ሽመልስ ሃብቴ ትምህርት ቤት ተመደብኩ፡፡ ጓደኝነታችን ግን ቀጠለ፡፡ ብርሃኑ ጎበዝ

ተማሪ ከመሆኑም በላይ በእኛ ትምህርት ቤት ልናገኛቸው የማንችላቸውን መጻሕፍት እየተዋሰ ስለሚያመጣልኝ አብረን እናጠና ነበር። አባቶቻችን በሁለታችን መቀራረብ ተደስቱ። በተለይ የእሱ አባት ‹‹ከአቶ ብሩክ ልጅ በስተቀር ሌላ ጓደኛ ጋር እንዳትውል›› ይሉት እንደነበር አጫውቶኛል።

የኔ አባት ቮልስዋገን መኪና ስለ ነበረችው አንዳንድ ቀን ሁለታችንንም ይዞን ይወጣ ነበር። አንድ ቀን ቤተ ክርስቲያን ሲሳለም ግቢ ገብርዔል ይዞን ሄደ። እኛም ከመኪና ወርደን ተከተልነው። ሁለታችንም ልክ እንደ አዋቂ በሥርዓት ተሳለምን፤ ሰገድን። ልባችንን ስብር አርገን ጸለይን። ለእኔም ለእሱም ለየት ያለ ልምምድ እንደሆነም ሳንነጋገር ተግባባን። እግዚአብሔር ልባችንን እያሰሰሰ ነበረ ማለት ነው።

1959 ዓም የሕዝብ ቆጠራ ተደርጎ ነበር። ቆጠራዉን ለሚያኪያሂደዉ ተቋም በክረምቱ ወራት ሥራ እንዲቀጥረን አመለከትንና ተቀበለን። ወደ ሥራ ከመግባታችን በፊት በንግድ ትምህርት ቤት በተዘጋጀዉ ሥልጠና ለመካፈል በሄድንበት አጋጣሚ ያገኘነው ክፍሌ አዋሽ የሚባል ጓደኛችን ልብ የሚሰቅል ወሬ ነገረን።



ብርሃኑ በለጋ ወጣትነት ዘመኑ

‹‹ተዓምራት ይደረጋል፣ አጋንንት ይወጣል፣ በሽተኞች ይፈወሳሉ፤ ለምን ሄዳችሁ አታዩም? ከፈለጋችሁ እኔ ቦታውን ላሳያችሁ. . .›› የሚል።





ክፍሌ አዋሽ ቦታውን ሲያሳየን ቀጠሮ ሰጠን። ቸርችል ጎዳና ቴዎድሮስ አደባባይ ዝቅ ብሎ በወንዙ አቅጣጫ ገደል ውስጥ የተመሠረተ ጸሎት ቤት ነበር። ክፍሌ አዋሽ ቀረ፤ እግዚአብሔር ቀድሞ ስለ ተገኘልን ሰዎች አጠያይቀን ቦታው ደረስን።

የዕለቱ አገልጋይ አበባ ረጋሣ ነበሩ። ልባችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከመፍሰሱ የተነሣ አገልጋዩ የሚናገሩት ሁሉ ያረሰርሰን ነበር። ‹‹ጌታን የምትቀበሉ›› ሲሉ እንደ ተመካከረ ሰው ሁለታችንም ተነሣን። ነሐሴ 26 ቀን 1959 ዓም ሁለንተናችንን ለመድኃኒታችንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስረከብን። እግዚአብሔር በልጅነታችን አገኘን።
ከዚህ ቀን በኋላ ብርሃኑ መንፈሣዊ ሩጫውን በርቀት ሲመራን እኔና ጓደኞቻችን ከማየትና እግዚአብሔርን ከማመስገን በስተቀር ልንደርስበት አልቻልንም። እሱ ልዩ ሰው ሆነ። *(ቃለ ምልልስ፣ አቶ ሚናስ ብሩክ - የልጅነት ጓደኛ)*

*ዶ/ር ብርሃኑ ይቺን የዳግም ልደታቸዉን ዕለት (ነሐሴ 26 ቀን 1959) በማስታወስ ከሃያ ስምንት ዓመት በኋላ በያዙት ዐውደ ዕለት ማስታወሻው ላይ ጠቅሰዋት ነበር። እንዲህ ሲሉ፦ ‹‹የልጅነቴ አምላክ ብቻዬን በነበርኩበት ጊዜ አገኘኸኝ።›› ለምን እንዳስታወሷት በኋላ እንመለስበታለን።*

## *3.2. የመሠራት ጊዜ:-*

*‹ብረት ብረትን ይስለዋል...›*

*ወደ ወጣትነት ዘመን ትረካ ተመልሰናል። የ1950ዎቹ የመጨረሻ ዓመታት ተጠቃሽ የሆኑ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴዎች በኢትዮጵያ ከተሞች ዙሪያ የተቀጣጠለበት*



ብርሃኑ በለጋ ወጣትነት ዘመኑ

ወቅት ነበር። ለዘመኑ ወንጌላዊውያን ክርስቲያኖች ‹‹ምስክርነት›› የሕይወት ዘይቤ ነበር። ወንጌልን ሳይመሰክሩ ከዋሉ በሕይወት መኖራቸውን የሚጠራጠሩበት ዘመን ነበር ለማለት ይበቃል። ወጣቱ ብርሃኑም የክረምት ሥራውን አጠናቆ በ1960 ዓ.ም መስከረም ወር ወደ ትምህርቱ ሲመለስ እንደ እርሱ ሁሉ በክርስቲያኖች ምስክርነት ተማርከው ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አርገው የተቀበሉ ወጣቶች በብዛት አገኘ። ከእነዚህ ወጣቶች ጋር ሕብረት እያረገ፣ እርስ በርስ እየተማማረ ዓመቱን አሳለፈ።

በ1960 ዓም ልክ በአሥራ ስድስት ዓመቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መልቀቂያ ፈተና ወሰደ። ሁሉንም ‹‹A›› አመጣ። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት ተሸላሚ ሆነ። በወቅቱ እጅግ ብርቅ የሆነው አንድ መቶ ብር አበል እየተሰጠው የዩንቨርሲቲ ትምህርቱን ለመከታተል ሳይንስ ፋክልቲ ገባ። በዚህን ጊዜም በክርስትና ሕይወታቸው እና በቀለም ትምህርት እንዲሁም በዕድሜያቸው ከእርሱ ይልቅ የበሰሉ እነ ተወልደ ዮሐንስ የመሳሰሉ ክርስቲያኖችን ለመተዋወቅ ቻለ።

ታላቁ መጽሐፍ ‹‹ብረት ብረትን ይስለዋል፣ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል›› (ምሣ 26:16) እንዲል ወጣቱ ብርሃኑ በባልንጀሮቹ ተሳለ። ስለቱም የተባ ሆነ። ወጣትነትን፣ የዩኒቨርሲቲ ትምህርትን፣ የግል ክርስቲያናዊ ሕይወትን፣ አገልጋይነትን አቻችሎ ጎን ለጎን ለማስኬድ ቻለ። በልጅነቱ ያሳለፈዉ የአገልግሎት ሀ - ሁ ሳያውቀዉ እስከ ፍፃሜዉ አብሮት ዘለቀ።





## 3.3. የአገልግሎት ሀ-ሁ . . .

ወጣቱ ብርሃኑና የዕድሜ እኩዮቹ መደበኛ የመሰብሰቢያ ሥፍራ አዘጋጅተው ቋሚ መንፈሣዊ አገልግሎት ለመስጠት ወላጆቻቸውን ጠይቀው የሚያገኟትን ፍራንክ እንዲሁም ዘመድ አዝማድ የሚልክላቸውን ተቆራጭ አጋጭተው በቅሎ ቤት አካባቢ ለጸሎት ቤት የሚሆን ቤት ለመከራየት ወሰኑ። በየግላቸዉና በሕብረት ሆነዉም ከአቅማቸዉ በላይ ማለትም ‹‹ከሌላቸዉ እንኳን›› ሰጥተዉ ጸሎት ቤቷን ለማደራጀት ተነሳሱ። ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ምስባክ ለማሟላት ሲጨነቁ ሰነበቱ።

መቼም ወጣትነት በልባምነት ሲባረክ ዓይነተኛውን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የነገሮችን ረቂቅ አካሄድ በዝርዝር ማገናዘብን እንዲሁም መመዝገብን ይወዳል። ታዲያም ልባሙ ብርሃኑ የጸሎት ቤቷን ገድል መመዝገቢያ በራሱ ገንዘብ ገዛ። ጥራት ያላት ‹‹ሪንግ ቡክ›› ነች። በዚያን ጊዜ ዋጋ ቢያንስ ሁለት ብር ሳታስወጣው አትቀርም። ልባቸው በወንጌል ፍቅር ከመንደዱ በስተቀር ሌላ ምንም ተሞክሮ ያልነበራቸው አቻዎቹ ያሳለፉትን ውጣ ውረድ፣ የእግዚአብሔርን ጥበቃና የዘመኑን መንፈሳዊ ሠልፍ በጥንቃቄ መዘገበባት። መግቢይዋ ላይም እንዲህ ሲል ጻፈባት፡-

> *‹‹እግዚአብሔር በተዓምራት የተሞላ አምላክ ነው። ተስፋው በፊታችን እየተፈፀመ ስለምናየው ተዓምራቱን ከማውራት ሥራውንም ከማወጅ አንቆጠብም›› እግዚአብሔር በየጊዜው የሚያደርገውን ድንቅ ሥራ በሙሉ ለብዙ ጊዜ ማስታወስ ስለሚቸግር ይህች ደብተር ለማስታወሻ እንድትጠቅም አዘጋጀኋት።* (መስከረም 1962)

ማስታወሻዋ ያልያዘችው ጉድ የለም። ጀማሪ አገልጋዮች በቅንነት ከሚፈፅሟቸው የዋህ ስህተቶች አንስቶ እግዚአብሔር ስህተቶችን ያረመባቸው የመንፈስ ቅዱስ ምሪቶች ሁሉ ተካተውበታል። ለወጣቱ ብርሃኑ እንደ ዋዛ መጥቶ እንደ ነፋስ የሚሄድ ነገር የለም። ለእሱ ሁሉም ክንውኖችና ትእይንቶች ቁምነገርና - ቁምነገር ብቻ ናቸው። እናም ማስታወሻዋ የልጅነት ሳቅና ስላቅ ከሚያመለክቱ ቃላትና አገላለጾች የፀዳች እንድትሆን አድርጎ የጸሎት ቤቷን ታሪክ መመዝገብ ጀመረ። በሌላ በኩል በአሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜው አካባቢ አንስቶ ማስታወሻዋ ላይ ያሠፈራቸዉ የጸሎት ቤቷ ዐውድ ዕለቶች የአዘጋጃት ብትሆንም ወደ አምላኩ እስከተሰበሰበበት ቀን ድረስ አጥብቆ የያዛቸው አስተምህሮዎች በማይነዋወጥ ሁኔታ በዘላቂነት የተመሠረቱት ገና በለጋነቱ እንደ ነበር ትመሰክራለች።

ስለ በቅሎ ቤቷ ጸሎት ቤት ከያዛቸዉ ከማስታወሻዎቹ አልፎ አልፎ ማስነበቡ የወጣቶቹን አገልግሎትና የብርሃኑን ጥንቁቅ አስተውሎት ለመረዳት ያስችላልና ‹‹እንደ ወረደዉ›› እነሆ፡-

**የመጀመሪያው ስብሰባ**

*ቅዳሜ መስከረም 10 ቀን 1962 ዓም የመጀመሪያው ስብሰባ ተደረገ። እኛ ተስፋ ከአደረግነው ቁጥር በላይ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ። የዕለቱ የመልእክት ክፍል ዮሐ 8፡ 36 — 37 ነበር። (ዐዉደ ዕለት10/1/62)*

**ፈውስ**

*ጌታ በመካከላችን ድንቅ ያደርግ ነበር በዚያው (ባለፈው) ሳምንት ውስጥ ከዳኑት ወንድሞች ውስጥ ሁለቱ የጸጋ ስጦታ ተቀብለው ትንቢት መናገር ጀመሩ። ሁለት ወጣቶች ከእርኩስ መንፈስ ነፃ ወጡ። አንድ ወንድም ደግሞ አንድ ጆሮው ደንቆሮ ነበር። . . .በእግዚአብሔር ክንድ ተከፈተ፤ ክብር ሁሉ ለእርሱ ይሁን!*

**ጠንቋዩ ተሰደደ**

*የጸሎት ቤታችን ባለበት አካባቢ እየጠነቆለ የአባቢውን ሕዝብ የሚያስት አንድ ሰው ነበር። ጸሎት ቤቱ በተከፈተ ሰሞን አንድ የሚሰያስደነግጥ ህልም አይቶ ለአንድ ክርስቲያን አጫወተው። ጠንቋዩ ያየዉ ህልም በአጭሩ፡- ትንንሽ ልጆች እየገረፉ ሲያሰቃዩት፤ በሽጉጥ ተኩሶ ሊገድላቸው ቢሞክርም መግደል እንደአቃተዉ። ሽጉጥ እየተኮሰባቸው እንኳን መግረፋቸውን እንደ አልተዉት ነበር። አሁን ይህ ጠንቋይ ሕይወቱ በጣም ስለ ተረበሸ ያንን ሠፈር ለቆ ወደ ሌላ ሰፈር ሄዷል። ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሁን! (መስከረም 3ኛው ሳምንት1962)*

**ልበ - ቅን ወንድሞች**

*ከጥቂቶች በስተቀር ወደ ጸሎት ቤቱ የሚመጡት አዳዲስ ክርስቲያኖች ነበሩ። እነዚህ ወንድሞች ብዙ ጊዜ እንደተለመደው (ተዘውትሮ እንደሚታየው) ሳይሆን ከመዝሙር ይልቅ ጸሎት በጣም ይወዱ ነበር። ለአንድ ሰዓት መንበርከክ ለእነርሱ ምንም አይመስላቸውም።*

*በዚህ አዲስ ፍቅር ውስጥ ሳሉ ሙሉ ጊዜያቸውን ለጌታ ሥራ ለማዋል በሕብረት ሆነው መመካከርና መጸለይ ጀመሩ። (ለጌታ ሥራ) እንወጣለን ካሉት ውስጥ እንዳንዶቹ ዕድሜያቸው ቢበዛ 15 ዓመት ነው። ለጌታ ሥራ ዕድሜን ይጠይቃል ማለቴ ሳይሆን የልጆቹን ልበ - ቅንነት ለማየት እንዲቻል ብቻ ነው። (ጥቅምት 1962)*

## የሌሊት ጸሎት

*ጸሎቱ ከታሰበው ጊዜ ይበልጥ ፈጀ:: ለማስቆምም ችግር ነበር:: ከዚህ በኋላ ግሩም ነገር ሆነ፤ በዚያ የነበሩት ወንድሞች አንድ በአንድ እየተነሡ መናዘዝ ጀመሩ:: . . . አንድ ወንድም ተነስቶ ‹‹እኔ አምላኬን በምግብ ለውጫለሁ:: ስለምግቤ ብዬ (ምናልባት ምግብ ጨምሩልኝ እያልኩ ማለቱ ይሆን?) ከቤተሰቦቼ እጣላ ነበር›› ብሎ ተናዘዘ (ሌላ ቅንነት)::*

*አንድ የተውሁት ነገር አለ በሦስተኛው የጸሎት ጊዜ ጌታ ትንቢት የሚያናግረው ወንድም የራሱን አፍ ተጠቅሞ ራሱን የሚገሥፅ ትንቢት ያናግረው ነበር:: ጌታ የተመሰገነ ይሁን! (ሐምሌ 16 ቀን 1962)*

## የማላውቀውን ተናገርኩ

*. . .በዚያ ሌሊት ጌታ በመካከላችን ከንዱን አጠንክሮ ነበር:: አንድ ወንድምና እህት እንደ ማይገባ እንደሚራመዱ ተገልጾ ነበር:: ወንድሞች ይህን አስፈሪ ሁኔታ በነገሩኝ ጊዜ እንደተደበደበ ሰው ትንፋሼ ቁርጥ ቁርጥ ይል ጀመር:: እነዚህ ወንድሞችም ከማሕበሩ ስለዚህ ጉዳይ መልእክት እንድሰጥ ጠየቁኝ:: በዚህ ጊዜ የነገሩን ከባድነትና የኔን ለዚህ ሁኔታ አለመዘጋጀት ሳይ ምን እንደ ምናገር አላወቅሁም ነበር::. . . እስከ መጀመሪያው የአንድ ሰዓት ከሩብ የጸሎት ጊዜ ምን እናገራለሁ ብዬ ሳስብ ነበር::*

*በዚህ ሀሳብ ውስጥ ሳለሁ ልቤ በጌታ ቅናት እንደ እሳት ይቃጠል ጀመር:: ወዲያውኑ በትልቅ የመንፈስ መቃተት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እያወጣሁ እንዴት እንደሚገጣጠሙም ሳላስብ በታላቅ ድምፅ መናገር ጀመርኩ:: በዚህ ሁኔታ ብዙ ከቀጠልሁ በኋል በውስጤ ይነድ የነበረው መልእክት አለቀ:: ጸጥ አልሁ:: ሰዓቴን ባየዉ - 5:30 ሆኖ ነበር:: (ሐምሌ 11 ቀን 1962)*





## አጉል ስምምድ

*በጥቅምት ወር 1963 ዓም ውስጥ የተለየ ነገር አጋጥሞን ነበር:: የስብሰባ ጊዜዎቻችን በእግዚአብሔር በረከት የተሞሉ ሆነው ሳሉ ክርስቲያኖች በተለይም የተወሰኑ እህቶች በጸሎት ጊዜ ወንበር እየገለበጡ መንከባለል ጀመሩ:: ስለዚህም አለመስተካከል ወደ ጌታ ጮህን:: ጌታም ሁኔታዉን ለወጠው::*

## ሐሰተኛ ጥሪ

*ጥቅምት 14 ቀን ስድስት ልጆች(ን) ጌታ ለሥራው እንደሚፈልጋቸው አንዲት ልጅ ትንቢት ተናገረች:: ‹‹ተለይተዉ የተጠሩት›› ልጆችም ወደ ቤታቸው እንዳይሄዱ ተነገራቸው:: ጸሎት ቤት ቆይተው ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን ወደ ቤታቸው ሄዱ:: ከሳምንት በኋላ ጥቅምት 21 ቀን 1963 እንደገና ተጠሩና ወደ ቤታቸው እንዳይሄዱ ማስጠንቀቂያ ተሰጣቸው:: ከተጠሩት መካከል ከሁለቱ በስተቀር አራታችን ለማደር ቆረጥን:: ‹‹እዚህ እደሩ ድንቅ ነገር አሳያችኋለሁ›› ተብሎ ተነግሮን ነበር:: የእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር እንዳይመጣብን እየገሠፅሁ እጸልይ ነበር:: ምንም ድንቅ ነገር ሳይደረግ ሌሊቱ አለፈ:: ስለ ተደረገው ነገር ምንም ፍርድ መስጠት አልቻልሁም::*

## ስደትና ፅናት

*በጸሎት ቤቱ ውስጥ ሦስት የተሰደዱ ልጆች ይኖራሉ:: (ቤተሰቦቻቸው) ከቤት ካባረሩአቸው ብዙ ጊዜ ሆኗል:: ፈፅመው ከቤት ያልተባረሩ ነገር ግን ብዙ መከራ የሚደርስባቸው ብዙዎች አሉ:: የአንዱን ሁኔታ እገልጻለሁ::*

*ወደ ጸሎት መምጣት ከጀመረ አንስቶ እንጀራ አባቱ ይደበድቡት ነበር:: ተደብድቦ (ጀርባው) ሰንበር ካወጣ ወዲያ*

*ከነሰንበሩ ጸሎት ቤት ይመጣል:: ወደ ቤቱ ሲመለስ ሰንበሩ ላይ ደግመው ይመቱታል:: አንድ ቀን ይብስ ብለው እናቱ (መጥተው) ከጸሎት ቤት ጎትተው እያወጡት በጥፊና በድንጋይ ይመቱት ጀመር:: በዚህ ዓይነት ከወሰዱት በኋላ ጥቂት ደቂቃዎች ቆይቶ እንደገና ወደ ጸሎት ቤት መጣ:: እንደዚህ ዓይነቱን ጥንካሬ ለሚታመኑበት የሚሰጥ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን! (ታህሳስ 1963)*

## ማስጠንቀቂያ ሆነልን

*በዚህ ሰሞን አንዲት ጠንቋይ ከኤስ አይ ኤም ማደ የጥንቆላ ሥራ ጀምራለች:: ዐርብ የካቲት 5 ቀን 1963 ዓም ሦስት ወንድሞች የጥንቆላው ሥራ ለማስተጓጎል ተመካክረው ወደ ቤቱ አካባቢዉ ሄዱ:: እነሱ ከመሄዳቸው በፊት በነበሩት ቀናት የመንደሩ ልጆች በጠንቋይዋ ቤት ላይ ድንጋይ እየወረወሩ ያስቸግሩ ነበር:: እነዚህ ወንድሞች በሄዱ ጊዜ ምናልባት ከድንጋይ ወርዋሪዎች ወገን ይሆናሉ ተብሎ ሳይጠረጥሩ አይቀርም በዛ ያሉ ሰዎች ሊደበድቧቸው ከበቡዋቸው:: ከመካከላቸው አንዱ ሮጦ አመለጠ፤ ሌሎቹ ሁለቱ ግን ተደበደቡ:: ከተደበደቡት ውስጥ አንዱ (የዕለቱን) የሌሊት ጸሎት መካፈል ቻለ:: ሌላው ግን በዱላው ደክሞ ነበር::. . . ጌታ ያለፍቃዱ ሄደን ሰሙን እንዳናሰድብ አስጠነቀቀን:: (የካቲት 5 ቀን1963)*

## እግራቸው ተሸከሟቸው ወጣ

*የጸሎት ስብሰባ ላይ ነበርን:: ወደ 11፡00 ሰዓት ገደማ በዛ ያሉ ጎረምሶች ወደ ጸሎት ቤቱ ተንጋግተው ገቡና አንድ ሁለት ጊዜ ወደ እነርሱ ጠጋ ስል ጫጫታውን ተዉና የምነግራቸውን ያዳምጡ ጀመር:: በኋላ ግን እርስ በርሳቸው ‹‹በሉ እንጂ ምን ተባብለን ነበር የመጣነው!?›› ይባባሉ ጀመር::*





*እኔ ግን - ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁኝ ወደ ውጪ እንድንወጣ ጠየቅኋቸው:: በአፋቸው ‹‹አንወጣም!›› ብለው መለሱልኝ:: እግራቸው ግን ተሸከሟቸው ከጸሎት ቤት ወጡ:: እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?*

## ስህተት የወሰደው በቀል

*. . .ከጸሎት ቤት ውጭ አንድ ወንድም ከተቃዋሚዎች አንዱን ይደበድብ ነበር! አድራጎቱ ያስቆጣቸው ሌሎች ተቃዋሚዎች በዚህ ወንድም ላይ ተከመሩበት:: ጥቂት ከተደባደቡ በኋላ ከረብሸኞቹ ግማሾቹ እንደ ገላጋይ በመካከል ገቡ:: ጥቂት ቆይተው - ደግሞ እርስ በርሳቸው መደባደብ ጀመሩና ያ ወንድም ተረፈ:: በተጠቀሰው ቀን የተደረገው ስህተት የበለጠ ችግር አመጣ:: ረብሸኞቹ በሚቀጥሉት ቀናት ተመልሰው መጡ:: ያ ወንድም ግን ተሸሽጎ አመለጣቸው:: በማግስቱ ግን በዱላ መደባደቡ የጌታ ፈቃድ እንዳልሆነ ያ ወንድም ተረዳ:: (መጋቢት 3 ቀን 1963 ዓ.ም)*

## ታላቅ ቀን

*ይህ ቀን ከአምላካች" አዲስ ሕይወት የተቀበልንበት ቀን ነው:: ከጌታ ጋር በውኃ ጥምቀት የተባበርን ከነፋስ ስልክ (በቅሎ ቤት?) ጸሎት ቤትና ከአዋሬ ጸሎት ቤት በአንድነት ተሰበሰብን:: የተሰበሰብነውም ስለ ቤተ ክርስቲያን መመሥረት የጌታን ቃል ልንሰማ ነው::. . .*

*. . .የጌታ ቃል ወደ ነፍሳችን እንደ ወለላ ዘልቆ ገባ:: . . . ስብሰባው ካለቀ በኋላ አንድ ላይ ተገናኘን:: ‹‹እንግዲህ ስለዚህ ነገር ምን እንላለን ተባባልን:: መልካሙን ሥራ በእኛ የጀመረው ጌታ ራሱ እንደሚፈጽመው በቃሉ ተስፋ ሰጠን:: (ቅዳሜ መጋቢት 25 ቀን 1963 ዓም)*

## 3.4. ከውጪ ወደ ውስጥ ማየት

ወጣቶቹ ከጸሎት ሕብረትነት ተነሥተው ወደ ክርስቶስ አካልነት (ቤተ ክርስቲያን) ከፍ እንዳሉ ተሰማቸው:: ከመካከላቸውም መጋቢዎችን ሾሙ:: አንዱም ወጣቱ ብርሃኑ ነው:: የአብዛኛዎቹ ዕድሜ፣ መንፈሣዊ ብስለትና ማሕበራዊ ዕውቀት (communal wisdom) ከሚፈቅደው በላይ ኃላፊነትን እንደ ተሸከሙ አይጠረጠርም:: በሌላ በኩል የእግዚአብሔር ቅንዓት እንደ እሳት የበላቸውና የወጣትነት አባዜ (Adolescence Syndrome) ማስተዋላቸውን እየዋጠባቸው እንደ አፈተታቸው የሚፈጥኑም ከመካከላቸው ነበሩ::

ከዚህም የተነሣ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፣ የቤተ ክርስቲያን አባልነት፣ የቤተ ክርስቲያን ግንኙነት ከማን ጋር? እንዴት? ለሚሉት ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሽ የመስጠትም፣ በምላሹ የመርካትም ነገር ብርቅ ሳይሆን አልቀረም:: ይህንን ነጥብ በተመለከተ በወጣቱ ብርሃኑ የዐውደ ዕለት ማስታወሻ ምንም ፍንጭ አይሰጠንም:: ነገር ግን በጊዜው ከነበረው መንፈሣዊ/ቤተ ክርስቲያናዊ ዐውድ በመነሣት አንዳንድ መለያየቶች ተፈጥረው እንደነበረ መገመት ይቻላል::

ያም ሆነ ይህ ከሰኔ 1964 እስከ ሐምሌ 1965 ዓም ድረስ ወጣቱ ብርሃኑ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ በሪፖርት መልክ የተወልን ምንም ነገር የለም:: ምናልባት ለራሱ ጭምር እንደገና ሊነግረው ያልወደደው ክስተት ይኖር ይሆን? ወይስ እግዚአብሔር ከጅምላው የፅዮን መንገደኛ ለይቶ ወደ ልዩ መንፈሣዊ ጥግ አድርሶት ይሆን? ወይንስ አምስተኛ





ዓመት የዩንቨርሲቲ ቆይታው ተግባራዊ ልምምድ የሚጀምርበት ወቅት በመሆኑ ጊዜ አጥሮት ይሆንን?

እርግጥ ነው የዐውደ ዕለቱ ማስታወሻ መያዝን የአኗኗር ዘይቤው አካል አድርጎታልና ከላይ በተጠቀሱት ጊዜያትም የሆነበትን - የሆነለትን መመዝገቡን አልተወም:: ማስታወሻዎቹ አጉልተው የሚያሳዩት እውነት ቢኖር በእነዚያ ሁለት ዓመታት ብርሃኑ ከውጭ ይልቅ ወደ ውስጡ የተመለከተበት ወቅት ነበር:: ይህንንም መንፈሱንና ነፍሱን እንደ ሰም ያቀለጡበትን የእግዚአብሔር ቃል መገለጦች፣ የመንፈስ ቅዱስ ድምፆች፣ ራዕይና መገለጦች ከሁሉም በላይ ደጋግሞ የሚያያቸው የማለዳ ሕልሞች፣ እንዲሁም በግል ከወንድሞች ጋር ባሳለፋቸው ቆይታዎች የተማራቸውን አዳዲስ ቁም ነገሮች ከመዘገበበት አዲስ የዐውደ ዕለት ጥራዝ መገንዘብ ይቻላል::

በጊዜዉ የያዛቸዉ ማስታወሻዎች:- በይዘት ረገድ ከዕለት የሕይወት ምሪት አንስተው አገር አቀፍ ገጽታ ያላቸው ትንቢታዊ መገለጦች ተካተውበታል:: ወጣቱ ብርሃኑ ከአሁኑ መሬት ረግጦ፣ በጥልቅ መሠረት ላይ ተመሥርቶና ከዓመታት በኋላ ሊገለጥ ባለው የኮሚዩኒዝም መንፈስና ዘመነ ደርግ ስደት ተዘጋጅቶ ሌሎችንም እንዲያዘጋጅ ሙጥኝ የሚሉቱ መልእክቶች ይበዙበታል:: ከኦርጅናሌዉ (እንደ ወረደ ከሆነው) አገላለፅ አንባቢውም በጥቂቱ ቢቃመስ ወደድን::

**መሬት እርገጥ!**

> *የጌታን ቃል ሳነብ ቆየሁና ለ7 ሰዓት ሩብ ጉይ ላይ ጌታን አመሰግኜ ጋደም አልኩ:: አይኖቼን እንደ ዘጋሁ የሚከተለውን መገለጥ አገኘሁ::*

*እግዚአብሔር ከመሬት ጥቂት ከፍ ከፍ አደረገኝ:: ከፍታዬም እየጨመረ ሄደ፤ በዚያን ጊዜ በልቤ ውስጥ የትዕቢት ደስታ ተሰማኝ:: እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ቃላት በውስጤ አልነበሩም:: ነገር ግን በዚያው በከፍታ ቦታ ሳለሁ ‹ይህ ያለሁበት (ሥፍራ) መንግሥተ ሰማያት አይደለምን?› እያልሁ እደነቅ ነበር::*

*. . . በኋላ እግዚአብሔር ቀስ በቀስ ዝቅ እያደረገ ወደ ታች ያወርደኝ ጀመር:: . . . ከዚያም አሮጌና የጨረጨሱ ቤቶች ወዳሉበት አሳረፈኝ:: እግሮቼ መሬት እንደ ረገጡ አንዲት ታናሽ ብላቴና መጣችና መሬት ይዣት (ወደ ላይ) እንድመጥቅ ለመነችኝ:: ተመለከትኳት ጥቂት ካመነታሁ በኋላ ‹ይህ ላንቺ አልተፈቀደም› ብዬ በኩራት መለስኩላት:: ከብላቴናይቱ ዘወር ብዬ እንደ በፊቱ ለመንሳፈፍ ስሞክር ያ ኃይል ከእኔ ሄዶ (ተወስዶ) አገኘሁት::*

*(ከዚያም) እፊቴ መንገዴ ላይ አንድ ሕፃን አጋጠመኝ:: ዘወር እንዲል ተናርሁት:: ልጁ ፊቱን በመቀየም አኮሳትሮ ትልቅ ድንጋይ አነሣብኝ:: አድራጎቱን በንቀት ተመለከትሁና ዛትሁበት:: በዚህን ጊዜ ሌሎች ሁለት ሕፃናት ተጨመሩና ከአቅማቸው የሚበልጥ ድንጋይ እያነሱ ሲወረውሩብኝ ድንጋዮቹ በሚያስፈራ ኃይል ወደ እኔ ይደርሱ ነበር:: እንደ ገመትኩት ሳይሆን በእነዚህ ሕፃናት ተሸንፌ ወደፊት መንገዴን መቀጠል አቅቶኝ ወደ ኋላ ተመለስሁ:: (ዐዉደ ዕለት 15/2/64 ሌሊት)*

**እያስተዋልክ ተራመድ!**

*የመድኃኒቴን ፈቃድ ለማወቅ በተሰበረ ልብና ዝቅ ባለ መንፈስ በፊቱ ተንበርክኬ ለማደር ወደ ፀሎት ሥፍራ ገባሁ:: የሰሞኑ ሁኔታ ልቤን አዝሎት ነበርና ነፍሴን ለጌታ አደራ ሰጥቼ ከእግሮቹ በታች አንቀላፋሁ:: ተለቅ ያለው የሌሊቱ ክፍል ካለፈ በኋላ ሕልም ተገለጠልኝ::. . .*





*በነቃሁ ጊዜ ነፍሴ በመንፈሴ ውስጥ ነበረች፤ አንድ ድምፅም ሁለንተናዬን ሞልቶ በሚያፅናና ስልት "Walk slowly, gently and evenly with lord" ይለኝ ነበር:: ከዚህ በኋላም አንቀላፋለሁ፤ እንደገናም ነቃሁ:: አሁንም ይህ ድምፅ ሁለንተናዬን ሞልቶ (ነበር):: እግዚአብሔር አጽናንቷታልና ነፍሴን ውኃ እንደ ጠገበ አትክልት ረካች:: (ዐዉደ ዕለት4/3/64)*

እግዚአብሔር እንዲህ እንዲህ እያለ፣ ብላቴናውን እያባበለ፣ ከውጭኛው ሁካታ እየጋረደ፣ ውስጡን በመንፈስ ቅዱስ ድምፅ እያቀና - እየሞረደ፤ እያበጃጀ ለታላቅ ሥራው ያዘጋጀዉ ጀመር:: ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ የዐውደ ዕለት ማስታወሻዎች ብቻ ወጣቱ ብርሃኑ ላቅ ወደ አለ መንፈሣዊ ልምምድና መለኮታዊ ምስጢራት ወደ መረዳት መሸጋገር የጀመረዉ ገና በለጋ ወጣትነቱ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል::

በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ብርሃኑ ከአደባባይ ውሎው እየታቀበና በራሱ የጸጥታ ድባብ እየፈጠረ መንፈስ ቅዱስን ለማድመጥ የቻለበት ሁኔታም ነበር:: ይኼዉም ከ1966 ዓ.ም አንስቶ ሊመጣ ያለውን ወታደራዊ ሥርዓት፣ መዘዙን፣ ሊያስከትል ያለዉን ስደትና የመበታተን ዘመን እንደሚሆን ገልፆለት ነበር:: ይህንን ምስጢር ለስንት ወገኖች አካፍሎ፣ ስንቶቹ እንደ ተቀበሉት እግዚአብሔር ነው የሚያውቀው:: እርሱ ግን እንዲህ አድርጎ መዝግቦታል::

**የመበታተንና የብቸኝነት ዘመን መጣ (ራዕይ)**

*በአንድ ሥፍራ ሆነን የተከፋፈሉ ሥራዎችን እንሠራለን:: ወንድም ------------ በእግዚአብሔር ቃል ሲገሥፀኝ አጠገቤ ነበር:: ይህንም በስሒተት (ያለ አግባብ) እንደ ሚያደርገው*

*ይታወቀኝ ነበር። ገና እንደ ጀመረ አንድ ሁኔታ ተፈጠረና አብረውኝ የነበሩት ሁሉ ሥራውን ለኔ አስረክበው ተበታተንን።*

*እቤቴ ውስጥ እንዳለሁ የተኩስ ድምፅ ሰማሁና ወጣሁ። በፊቴ አንድ ስታዲዮም ይታየኛል። በጫወታው የሚካፈሉትና አስተናባሪ የነበሩት ወታደሮች ናቸዉ። ነገር ግን በመካከላቸዉ መለያየት ሆነና እርስ በርሳቸው እያንዳንዱ ወገን በሌላዉ ላይ ጦር ያስከትት ነበር። ከተማውም በአጠቃላይ ለትልቅ ጦርነት ይዘጋጃል። እያንዳንዱ ሰውም ለራሱ መሣሪያ ይይዝ ነበር።*

*እኔም በውስጤ እነዚህ ሰዎች በኛ ላይ ክፋት ስለ ሠሩ አሁን የእርስ በርስ ጦርነት ሆነባቸው እያልሁ ወደ ቤቴ አመራሁ። እቤት (ስደርስ) ኮረንቲ ጠቅላላውን ጠፍቶ ስለ ነበር ኩራዝ ተለኩሶ ነበር። በልቤ ብዙ ሻማ መግዛት እንደ ነበረብኝ በቂ ገንዘብም እንዳለኝ ይታወቀኝ ነበር። ደግሞም ለረዥም ጊዜ ተለያይተን እንደምኖር ይታወቀኝ ነበር። (ዐዉደ ዕለት8/10/64)*

**ከዚያም ትንቢታዊ ድምፅ መጣልኝ**

> *‹‹እኔ እመራችኋለሁ፤ በየእለቱ እመራችኋለሁ መንገዳችሁም ጭለማ አይሆንም። ከምታዩትና ከምትሰሙት ነገር የተነሣ አትደንግጡ። አታመንቱ፣ አትወናበዱ፣ የዘመኑን ምስጢር (እኔ) እገልጥላችኋለሁ . . .።››*

እኒህን በመሰሉ መንፈሣዊ መገለጦች፣ ትንቢቶችና ምሪቶች ውስጡን እየከረከመ በውጪም የዘመኑን ሁኔታ እየገመገመና ከወገኖች ጋር ኅብረት እያደረገ የአምስተኛ ዓመት የዩንቨርሲቲ ትምህርቱን አጠናቆ ለክረምት ዕረፍት ተዘጋጀ።





መቼም ለዚያን ዘመን ክርስቲያን ተማሪዎች ዕረፍት ማለት ጌታን ማገልገል ነውና - ወደ ሁለት ወራት የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ተሰማራ ማለቱ ይሻል ይሆናል። በዚህ ወቅት ስለ አለፈበት የአገልግሎት ሀ - ሁ እንዴቱና ምንነቱን እንዳናውቅ አድርጎናል። ነገር ግን የስድስተኛ ዓመት የዩንቨርሲቲ ትምህርቱን መስከረም ወር 1965 ዓም ከመጀመሩ በፊት ትሁት ልቡናው ሊሸከመው የማይችለው ራዕይ ተገለጠለት፤ ትሁት ነፍሱን የሚያንቀጠቅጥ የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ በውስጡ አለፈበት። ድምፁም በቀጣዮቹ ሃያ አራት ዓመታት ያልተቋረጠ፣ እያደር የሚጎላ፣ እያደር የሚደምቅ፣ እያደር የሚብራራ ሆኖ የሚከታተለው ድምፅ ሆነበት፤ ሆነለትም።

# 4. አገልጋይ ብርሃኑ

## *4.1. የመጀመሪያ ጥሪ - 1964*

እግዚአብሔር ለሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይነት እንደ ሚፈልገው ለመጀመሪያ ጊዜ በግልፅ ራዕይ ለራሱ የተናገረው ሐምሌ 13 ቀን 1964 ዓ.ም ነበር። ልባሙ ተማሪ እንደሚከተለው መዝግቦታል።

> *“ . . .መልእክት በደብዳቤ እጽፍ ነበር። ይልቅስ እንዳይበላሽብህ ደህና አድርገህ ቅረፅ አለኝ።. . . የምፅፈው ቃል ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ይባላል የሚለውን ነበር። በመንፈስ ውስጥ ሆኜ ሳስታውስ የኢትዮጵያ ካርታ ፊት ለፊቴ ታየኝ። እኔም ለኢትዮጵያ መልእክተኛ እሆናለሁ ማለት ነው እንዴ? ብዬ ጠየቅሁት።*
> *‹ . . . እንግዲያውስ ልንገርህ አንተ አገር አቀፍ (የወንጌል) ጥሪ አለብህ። ስለዚህ ክበደል ራቅ› አለኝ።›› (ዐውደ ዕለት ማስታወሻ ሐምሌ13 ቀን 1964)*

ይህንን ታላቅ መልእክት ከተቀበለ በኋላ ቀጣዮቹን ሁለት ዓመታት የበለጠውን ጭምት፣ የበለጠውን ዝምተኛና ምስጢረኛ ሆኖ አሳለፈ። በእነዚህ ጊዜያት ቀደም ሲል በራዕይ ተገልጠውለት የነበሩት የአገር ያለ መረጋጋትና የሕዝብ ሰላም መታወክ፣ እንዲሁም በወገኖች ዘንድ በጥቃቅን ያለ መግባባቶች ምክንያት የመለያየትና የመበታተን ዘመን የዋዜማው ምልክቶች እየታዩም ነበር።

በተለይም የ1966/67 ዓ.ም ሕዝባዊ ተቃውሞን ተከትሎ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት መፈራረስ፣

የደርግ መቋቋምና በደርጉ አባላት መካከል ቀስ በቀስ የተፈጠረው መጠላላትና መገዳደል በተለይም ሙሉውን የወጣት ትውልድ ክፉኛ የተጠናወተው የክህደት (ኮሚዩኒዝም) መንፈስ አገሪቱን የሚንጥበት ወቅት ጋር ጥሪዉ መገጣጠሙ ሸክም ሆኖበት ነበር። ብርሃኑ የሕክምና ትምህርቱን አጠናቀቀና በ1966 ዓም መጨረሻ ተመርቆ ለተከታዮቹ ሃያ አራት ዓመታት ሊቆይበት ወዳአሰዉ የሥራ ዓለም የተሰማራውም በዚሁ ጨፍጋጋ የዘመን ዐውድ መባቻ ላይ ነበር።
እኛም እንግዲህ ወጉ ያስገድደናልና እርሰዎ እያልን ልንዘክረዉ ነዉ።

## 4.2. የመጀመሪያዉን ጥሪ የተጫጫኑት አዮራት

ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ የመጀመሪያውን ጥሪ ከተቀበሉ ከ3 ዓመት በኂላ በ1967 ወደ ሥራ አለም ተሠማሩ። ወቅቱ አገሪቱ በአብዮት ምጣድ ላይ የምትንገረገብበት የዘመን መባቻ ነበር። እሳቸዉና እንደ እሳቸው ያሉ ለወንጌል አገልጋይነት የተስፋ ቃል የተቀበሉ ሁሉ የተስፋቸው ተቃራኒ የሆነ ድርጊት ዕለት በዕለት ሲፈፀም ሲመለከቱ በጥርጥር ማዕበል መንገላታታቸው መቸም አይቀርም።

አዲስ አበባ ተወልዶ የአደገ፣ የተማረና ሁለመናው *አዲስአቢኛ* ሆኖ ባሌ ክፍለ ሐገር (አንዳንድ የወቅቱ ታዛቢዎች ባሌን ሌሊንግራድ የሚል ቅፅል ስም አዉጥተዉላት ነበር) ለተመደበ ክርስቲያን ዶክተር ደግሞ ሕይወት እንደ ክፉ ቅዠት ያስደነብር ነበር። ስለሆነም ዶ/ር





ብርሃኑ የተቀበሉት ራዕይና አዲስ አበባ ፈንድቶ ባሌ ጎባ የሠከረው አብዮት እውነታ እንደ በጠበጣቸው አያጠራጥርም (ዝርዝሩን በምዕራፍ አምስት ይመልከቱ)። ከዚህም የተነሣ ይመስላል በአሥራ ሰባቱ የአብዮት ዘመን ለሙሉ ጊዜ አገልጋይነት መጠራታቸውን በተመለከተ የተብራራ ማስታወሻ የአልተዉልን።

አልፎ አልፎ ግን ጭለማውን እየገመሰ ከማዕዘን ወደ ማዕዘን እንደ ሚወረወር ኮከበ - ብርሃን ጥሪቸያውን የሚያፀኑ መልእክቶች ይቀበሉ ነበር። የቃል ኪዳን ልጁን ሲጠብቅ የዕድሜ ቁጥሩ መቆለል ተስፋ አስቆርጦት ‹‹እኔም ያለ ልጅ እሄዳለሁ›› እያለ ሲያጉተመትም እግዚአብሔር ብቅ እያለ እንደሚያፅናናው ልክ እንደ አብርሃም፤ ዶ/ር ብርሃኑንም በጠንካራ የቃላት አገላለፅ ብርቱ የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ‹‹አይዞህ!›› ይላቸው ነበር። ለምሳሌ እንደሚከተለዉ፦

> *‹‹በአዳር ጸሎት ላይ ነበርሁ (ብቻዬን)። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ በግል የጌታን ክብር መገለጥ እየተጠባበቅሁ ቆይቻለሁ። በዚህ ዕለት ስለ መንገዴ የእግዚአብሔርን መመሪያ ፈለግሁ። ተንበርክኬም ሳለሁ እንደሚከተለው ተገለጠልኝ።*
>
> *እኔ ተንበርክኬ ሳለሁ በጭለማ ውስጥ በፊቴ የአንድ ሰው ፊት (ገጽታ) ታየኝ። . . . የዚህ ሰው ስም ስምዖን እንደሆነ ታሰበኝ። ወዲያውኑ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ያለው ስምዖን እንደሆነ ተረዳሁ። መልእክቱም ይህ ነበር።*
>
> *እነሆም በእየሩሳሌም ስምዖን የሚባል ሰው ነበር። ይህም (ሰው) የእሥራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር፤ ጻድቅና ትጉህም ነበር። መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበር። በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ*

*ነበር (ሉቃስ 2:25 26)። (ዐዉደ ዕለት መስከረም 24 ቀን 1966 ዓም)*

የመልእክቱን ይዘት በአንድ ዓረፍተ ነገር ያጠቃለሉት ***‹‹የስምዖን ዕድል ፈንታ ለእኔም ይሆናል››*** በማለት ነበር።

በእርግጥም ዶ/ር ብርሃኑ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መጽናናትንና በአጠቃላይም ምድሪቱ ከክህደት መንፈስ ፀድታ ለወንጌል ሥራ ምቹ የምትሆንበት ዘመን እንደሚመጣ ተረድተው ነበር። እስከዚያች ቀን ድረስ ለትምህርት ወይም ለሥራ በተላኩባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ከትምህርት ወይም ከሥራ ውጭ ያለውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ስደተኛዋን ቤተክርስቲያን በማገልገል፣ ወገኖችን በማፅናናትና በማሰባሰብ ነበር።

እዚህ ትረካ ጫፍ ላይ ስንደርስ ከዋና ርዕሰ ጉዳያችን ወጣ ለማለት ልንገደድ ነዉ፤ ለአንባቢዉ የአዕምሮ መደላድል የሚሆኑ ታሪካዊ ክስተቶችን ለመዳሰስ ስንል። በተለይም የደርግ ዘመን ተብለው ከሚታወቁት 17 ዓመታት ወዲህ ነፍስ ያወቁ ወገኖችን አይገርምም። ‹‹***የኮሚዩኒዝም መንፈስ፣ ስደተኛዋ ቤተክርስቲያን፣ ወገኖችን ማፅናናት፣ በህቡዕ ማሰባሰብ፤ ብሎ ነገር ምን ማለት ነው?***›› ማለታቸዉ አይቀርምና። በሁለተኛ ደረጃም የዚያን ዘመኑን ውክቢያ፣ ሹካታ፣ መንፈሣዊ/ሥጋዊ ትርምስ በአጭሩ መግለፁ ባለ ታሪኩ ያለፉበትን ማህበራዊ ዐውድ፣ መንፈሳዊ ዉጊያ፣ የከፈሉትን ዋጋና የህይወት ጥንቃቄና ፅናት ወለል አርጎ ያሳያልና እነሆ!





# 5. ዘመነ መብሰክሰክ (1967- 1983)

## *5.1. ክርስቲያን ሰው ነው*

ክርስቲያን ሰው ነው፤ ክርስቲያን የአንድ አገር ዜጋ ነው፤ ክርስቲያን ተወልዶ ያደገበት ማሕበረሰብ አባል ነው። ክርስቲያን በክፉም ሆነ በደግ፣ አገሩ ወይም የገዛ ማሕበረሰቡ በሚያልፍበት ውጣ ውረድ ውስጥ ድርሻ አለው። ለክፉም ሆነ ለደግ በሚከናወኑ ሁኔታዎች፦ አዕምሮው፣ መንፈሱ፣ ስሜቱና ፈቃዱ ይነካል፤ ሰው ነውና። ከዓለሙ ሁለመና ተገንጥሎ ለብቻው የቆመ ፍጡር አይደለምና።

ይህ ክፍል ዶክተር ብርሃኑና ዘመነኞቹ እንዲሁም የዚያን ዘመን ትውልድ አባላት የነበሩ ክርስቲያኖች ያለፉባቸዉን አጠቃላይ ሁኔታዎችንና ከዚህም የተነሣ በእምነታቸው፣ በአመለካከታቸውና በማሕበራዊ ሕይወታቸው ላይ ያረፉትን መልካምና መልካም ያልሆኑ ተፅዕኖዎች በአጭሩ ለመግለፅ ያለመ ነው።

### *የሥርዓተ ዘውድ- ፍፃሜ*

የሰሎሞን ሥርወ መንግሥት 252ኛው ንጉሥ የነበሩት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ 80ኛ አመት ልደታቸውን ሐምሌ 16 ቀን 1964 ዓ.ም አከበሩ። የነፃነትና የጥቁር ሕዝብ ኩራት ምልክት አድርጎ የሚቆጥራቸው መላው የአፍሪካ አኅጉር ልደታቸውን አከበረ። ዝናቸውን ለመዘርዘር ሲባልም በርካታ